# መጽሐፈ አስቴር

፩

## መቅድም

አስቴር የተናገረችው ነገር ይህ ነው፤

አስቴር ማለት ፀሐይ፤ አንድም ሠረገላ ፀሐይ ማለት ነው፤ ይህስ እንደምን ነው ቢሉ አርጤክስስ የሚባል የፋርስ ንጉሥ ነበር፤ መቶ ኸያ ሰባት አህጉር የሚገዛ፣ ለመቶ ኸያ ሰባት አህጉር መቶ ሰማንያ ስምንት ቀን በአዳራሽ ተገኘ፤ መቶ ሰማንያውን ለመላው፣ ስድስቱን ቀን በከተማ ሳሉ፣ ሁለቱን ቀን ለቋሚ ለለጓሚ ይገኝ ነበር፤ ከዕለታት አንድ ቀን በአዳራሽ ተገኝቶ ሲአበላ ሲአጠጣ ሚስቱ አስጢን ትባላለች፤ ነዪ ብሎ ላከባት፣ ስለምን ቢሉ ፈቃድ ተነስቶበት ይህስ ጊዜውም አይደል ብሎ መልከ መልካም ነበረችና መልኳን ለማሳየት፤ አንድም እቴጌነት አላደረሰላትም ነበርና እቴጌነት ለማድረስ እሷም ከሱ አስፈቅዳ በአዳራሽ ተገኝታ ነበረችና አልመጣም ብላ ላከችበት፤ ከዚያ የተቀመጡ መኳንንቱ የአንተ የንጉሡ ሚስት ብትልክባት እንቢ ያለች የኛማ ሚስቶች ሽሮ ጠብሰው፣ ጣቢታ አፍሰው ይሰጡናልን፤ ፍታት አሉት፤ ፈታት ንጉሡን ሚስቱን፤ አስፈትተን ዝም እንላለን ብለው ከመቶ ኻያ ሰባቱ አህጉር ሽሕ ሴት መረጡ፤ ከሽው መቶ፤ ከመቶው አሥር፤ ከዐሥሩ ሦስት መረጡ ሦስተኛ ይቱ፤ አስቴር ናት፤ የመርዶክዮስ የአጎቱ ልጅ ናት፤ ወአልሐቃ ከመ ትኩኖ ወለተ፣ ልጅ ትሆነው ዘንድ አሳደጋት፤ አንድም ብእሲቶ ይላል፣ ሚስት ትሆነው ዘንድ አሳድጓት ነበር፤ እንደ ዛሬ ሥርዓት አልጸናምና አሕዛብ ፈጥነው አይደርሱም፤ መንፈቅ የላዩን ገላ የሚያጠራ፣ መንፈቅ የውስጡን ገላ የሚያጠራ ሽቱ እየቀቡ፣ መጠጥ እየአጠጡ ይቀመጣሉ፤ ጋይ የሚባል ጠባቂ ሰጥቷት ተቀመጠች፤ በዓመቱ ሰርግ አደረገ፤ ለነዚያ ሦስት ቀን፤ አራት ቀን ሠርግ አደረገላቸው ወአዕበዮ ለመርዓ አስቴር እንዲል፣ ለሷ ግን ሰባት ቀን ሠርግ አደረገላት ፤ ደረሰባት ፤ ወደዳት መርዶክዮስ በሷ ምክንያት እንደ ጸበል ረጭ ሆኖ ገባ፤ በመርዶክዮስ ቀናን ያሉ ታራ ገቦታ ንጉሡን በጫማው የባብ መርዝ ሰፍተን እንግደለው

www.ethiopianorthodox.org

ብለው መከሩ፡ እንድም እንደ
ንስናሽ ያለ አድርገን እንግደ
ለው ብለው መከሩ፡ መርዶ
ክዮስ ይኽን ሰምቶ ለአስቴር
ነገራት፡ አስቴር ለንጉሡ
ነገረችው፡ ንጉሡ አስጠርቶ
ቢጠይቃቸው አዎን አሉ፡
አሰቀላቸው ሐማ ስለዚህ ነገር
አዘነ፡ ስለምን ቢሉ ዘመዶቹ
ናቸውና፡ አንድም በነገሩ ነበረ
በትና ከንጉሡ ዘንድ ገብቶ
ንጉሥ በመቶ ኻያ ሰባት
አህጉር ያሉ ጠላቶችህን ላጥ
ፋልህ፡ እልፍ ወርቅ ልስጥህ
አለው፡ ጠላቶቼን ብታጠፋ
ልኝ ወርቅ ለኔ ምኔ ነው፡
ወርቅከኒ ይኩን ለከ፣ ወርቁ
ብሩ ላንተ ይሁንህ፡ ሕዝበኒ
ግበር በከመ ፈቀድከ ጠላቶ
ቼን ግን እንደ ወደድህ
አድርግ አለው፡ ፈላስፋ ነበርና
ከተራራ ላይ ወጥቶ ከቀን ቀን
ቢያወጣጣ እስራኤል የሚጠ
ፉበት በመጋቢት በ፲፬ ቀን
ተገለጸለት፡ በመቶ ኻያ ሰባት
አህጉር ያሉ እስራኤልን አጥፉ
የሚል ክታብ ጽፎ ሰደደ፡
መርዶክዮስ ይኽን ሰምቶ
አስቴር ካለችበት ሂዶ አጨበ
ጨበ ፡ አክራትዮስ የሚባል
ባለሟል ነበራት ሰደደችለት፡
እኔ እንዳልገባ ልብስ አለበስ
ሁም አለው፡ ልብስ ልስደድልህ
ብላ ላከችበት፡ አይሆንም
አልገባም አላት፡ እንግዲያስ
ላክብኝ አለችው፡ ይህ መንግ
ሥት ቁም ነገር አይምሰልሽ፣
ዘመዶችሽ እስራኤልን ሐማ
ለእልፍ ወቄት ወርቅ ብር
ሽጣቸው ለዚህ ነገር እወቂበት
ብሎ ላከባት፡ እሷም አንተም
እዘንበት፣ እኔም አዝንበትአ
ለሁ ብላ ላከችበት ፡ ከዚህ
በኋላ ቀኖና ገብታ ነገር
አግኝታ፣ ተኩላ ተቀብታ የም
ትወዳትን ገረዷን በኋላዋ፣
የምትጠላትን በፊቷ አድርጋ
ሄደች፡ ዓይነ ወርቅ ነበረበትና
በዚያች በምትጠላት እንዲ
ያርፍ፡ አንድም የምትጠላትን
በኋላዋ፣ የምትወዳትን በፊቷ
አድርጋ ሄደች፡ ከበትረ ወርቁ
ይትረ ፋት ብላ ሲያያት
ስልቅልቅ ብላ ወደቀች ፣ ልቡ
ናውን ወደ ርኅራኄ መለሰ፡
በበትረ ወርቁ ነካ ነካ አደ
ረጋት፡ ተነሳች፡ የኛ እንጅ
የነገሥታቱ ሚስቶች ሳንልክ
ባቸው አይመጡም ለምን
መጣሽ አላት፣ ነገር አግኝቶኝ
ልነግርህ መጥቻለሁ አለችው
በይ ንገሪኝ አላት፡ ነገ ምሣ
የማደርግ ነኝ ከምሳው እንድ
ትመጣልኝ፣ ሐማም እንዳይቀ



ርብኝ ነገሩን ከዚያው እነግርህ
አለሁ አለችው፡ ይሁን ብሎ
ሰደዳት፡ ከዚህ አስቀድሞ፡
ዘኢሰገደ ለሐማ ይትበርበር
ቤቱ ወይትኰነን ነፍሱ ብሎ
አዋጅ ነገረለት፡ ሁሉ ተገዛ
ለት፣ ሁሉ ሰገደለት፣ መርዶ
ክዮስ ሳይሰግድለት ቀረ፡
ዘሰገደ ለፍጡር ርጉም ውእቱ
ትላለችና አሪት፡ በዚህም ቀን
ከምሳው መጡ፡ በዪ ንገሪኝ
አላት፡ ነገም ምሳ የማደርግ
ነኝና እንድትመጣልኝ፣ ሐማም
እንዳይቀርብኝ አለች፡ ሐማም
ከቤቱ ሂዶ ተሸፋፍኖ ተኛ፡
ሚስቱ ሳራ ዙማሬ ትባላለች፡
ንጉሥ፣ ንግሥት ተጣልተው
ህልን ወይስ ከምሳው አልተጠ
ራህም አለችው፡ ንጉሥ ንግሥ
ትም አልተጣሉኝ ከምሳውም
ያለኔ የተጠራ የለም አላት፡
ነገር ግን ሁሉ ሲሰግድልኝ
መርዶክዮስ የሚባል አንድ
አይሁዳዊ ሳይሰግድልኝ ቀረ
አላት፡ ለዚህማ በመቶ ሃያ
ሰባት አህጉር ያሉ እስራኤልን
አጥፉ ያለህ እሱን ብትገድለው
ዕዳ ይልብሃልን አለችው፡
ቢቸኩል ኃምሳ ክንድ ተራዳ
ተክሎ አደረ፡ ወነፍጸ ንዋም
እምዓይነ ንጉሥ ይላል፡ በዚህ
ቀን ንጉሡ እንቅልፍ አጥቶ
ወግ ታሪክ ሲያይ አደረ፡ ዛሬ
የኛ ነገሥታት ወግ ታሪክ
ሲመለከቱ እንዲያድሩ ያን
ጊዜ ሲነበብ፣ ሲተረጐም ታራ
ገቦታ እንደ መከሩበት መርዶ
ክዮስ እንዳዳነው ከተጻፈበት
ደረሰ፡ አንድም በተአምራት
በመጀመርያ ወጣ፡ ለዚህ ሰው
ምን አድርጌለትአለሁ አለ፡
ምን አድርገህለታል፣ እንደ
ጸበል ረጭታ ሁኖ ተቀምጦአል
እንጅ አሉት፡ ሐማ ምንስ
ሁሉን አጥፋ ቢለኝ ሳያስና
ብተኝ እገድለዋለሁን ብሎ
ገሥግሶ ሄደ፡ ንጉሡ ነጐዳ
ሰምቶ ማነው ብሎ ጠየቀ፡
ሐማ ነው አሉት፡ ግባ በሉት፡
አለ ገባ ፡ ሐማን ንጉሡን
ከሞት ላዳነ ንጉሥ ለወደደው
ምን ሊያደ ርጉለት ይገባል፡
ምን ጊዜስ ያለኔ ምን ወዳጅ
አለው ብሎ በንጉሡ በቅሎ
አስቀ ምጦ፣ ከሩር ደፍቶ፣
ከሩር አልብሶ ሁሉን ግዛ ንዳ
ብሎ አዋጅ ሊነገሩለት
ይገባል አለው፣ ዘንተኒ ግበር
ሎቱ ለመርዶክዮስ

ወኢታትርፍ ቦቱ ምንተኒ

ይህን ሁሉ ለመርዶክዮስ አድር
ግለት ምንም ምን አታስቀርበት
አለው፡ የንጉሥ ትእዛዝ አይቀ

www.ethiopianorthodox.org

ርምና በንጉሡ በቅሎ አስቀ ምጦ ከፋር ደፍቶ፣ ከፋር አልብሶ ሁሉን ግዛ ሁሉን ንዳ ብሎ አዋጅ ነገረለት፤ በዚህም ቀን ምሳ አድርጋለችና ከምሳው መጡ፤ በዩ ንገሪኝ አላት፤ ሰው ይመለስልኝ አለችው፤ ሰው ተመለሰ፣ በይ ንገሪኝ አላት፤ ምነው በእልፍ ወርቅ የሸጥኸን አለችው፤ ማን አለሽ አላት፤ ዝኩ ጸላዒነ ሐማ አማሌቃዊ፣ ይህ ጥንተ ጠላ ታችን ሐማ ነው አለችው፣ መልስ ሳይመልስላት ተክል ለማየት አንበሳ ቤት ለመቀ መጥ ወጣ፤ አንድም እጃቸውን እግራቸውን እየፈ ተኑ ይጠ ጣሉና በዚህ ጊዜ ሐማ በጥግ ሁኖ ይሰማ ነበር፤ ገብቶ ይህን እልፍ ወርቅ ላንች ልስጥሽ አንች የሰቀልሽውን አንች አውርጅው ብሎ ከእግሯ ወደቀ፤ ንጉሡ ቢመለስ ከዚያ አገኘው፤ ብእሲትየኑ ትትኤ ገለኒ በቤትየ ፤ ሚስቴን በቤቴ ልትቀማኝ ነው? አለው፤ ወጸልመ ገጹ ለሐማ እንዲል፣ ፊቱ ጠቆረ፤ ቡክታር ቡክታን የሚባል ሰይፍ ጃግሬ ነበረው፣ ንሣ በሰይፍ በለው አለው፤ ካልክስ ለመርዶክዮስ የተከለው ተራዳ አለ አለው፣ ወስደህ ስቀ ለው አለው፣ ወስዶ ሰቀለው፤ ከዚህ በኋላ መርዶክዮስ ለንጉሥ ነግሮ በመቶ ኸያ ሰባት አህጉር ያሉ እስራኤል ይዳኑ የሚል ክታብ ሰደደ፤ በመጋቢት በ፲፬ ቀን ሊጠፉ የነበሩ፣ እስራኤል በተአምራት በአሥራ ሦስተኛው ቀን ደርሶላቸው ድነዋል፤ ይኸኑንም የዳኑበትን ቀን ባመት ባመት አንዳንድ ግንዛ ጥጥ እየተኮሱ ያከብሩት ነበር፤ እሰቀላለሁ ያለ መርዶክዮስን ያዳንህ፣ እሰቅላለሁ ያለ ሐማን ያሰቀልህ አንተ ነህ ሲሉ፣ ይህም ተጻፈ፣ ተጽፎ ሲነበብ፣ ሲተረጐም ከነቢያት እስከ ሐዋርያት ደረሰ፤ ሐዋር ያት ሰማንያ አንዱን መጻሕፍት ለቀሌምንጦስ ቆጥረው ሲሰጡ አንድ መጽሐፈ አስቴር ብለው ቆጥረው ሰጥተውታል፤ ይህም ለከንቱ አልተጻፈም፤ እኛ ልንመከርበት፣ ልንገሥጽበት ነው እንጂ፤ ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጸ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትእግሥትነ ወበተወክሎተ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ እምኀበ እግዚአብሔር እንዲል፤ ይህ አርስት ነው፤ ነገሩን በካልዕ ዓመት ብሎ ያመጣዋል፤

[stamp] ...ት ሬታና ቤተሰቧ የግል ቤተ መጻሕፍት



## ምዕራፍ ፩

፩፡ በካልዕ ዓመት እምዘ ነግሠ አርጤክስስ ዓቢይ፣

የገንዘብ ነው፣ አርጤክስስ በነገሠ በሁለተኛው ዘመን፤

አመ ቀዳሚት ዕለት ዘኔሳን፣

በመጀመሪያው ወር በሚያዝያ ዘኒስካ ቢል በዓለ ፋሲካ በሚደ ረግበት በመጀመርያዪቱ ቀን፤

ርእየ ሕልመ መርዶክዮስ ዘኢያኤሩ፣

የኢያኤሩ ልጅ መርዶክዮስ ሕልም አየ፤

ዘሴምዩ፣

ኢያኤሩን የሴምዩ ልጅ አለው፤

ዘቂስዩ፣ ዘእምነገደ ብንያም፤

ቂስዩን ከብንያም ወገን የተወ ለደ አለው፤

፪፡ ብእሲ አይሁዳዊ ዘይነብር ውስተ ሱሳ፤

በሱሳ የሚኖር አንድ አይሁዳዊ ነበር፤

ወዓቢይ ብእሲሁ ውእቱ፣

ሰውየው ደግ ነበር፤

ወይነብር በዐፀደ ቤተ ንጉሥ፣

በቤተ መንግሥት እንደ ዐበል ረፊ ሁኖ ይኖር ነበር፤

፫፡ ወእምነ ፄዋ ውእቱ ዘፄወዎ ናቡከደነጾር ንጉሠ ባቢሎን እምኢየ ሩሳሌም ምስለ ኢኮንያን ንጉሠ ይሁዳ፣

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ከይሁዳ ንጉሥ ኢኮንያን ጋራ ከኢየሩሳሌም ከማረካቸው ምርኮ ወገን ነው፤

፬፡ ወዝንቱ ውእቱ ሕልሙ፣

ሕልሙም ይህ ነው፤

ወናሁ ቃል፣

ተሰምዓ ያለበት ነው፤ እነሆ ቃል ተሰማ፤

ወሁከት፣

ሽብር ሆነ፤

ነጐድጓድ ወድልቅልቅ፣

ነጐድጓድ ንውጽውጽታ ሆነ፤

ወገሩ ጉአ ላዕለ ምድር፣

በምድር ላይ ችኮላ ሆነ፤

፭፡ ወናሁ ፪ቱ አክይስት ድልዋን፣

እነሆ የተዘጋጁ ሁለት ታላላቅ ዘንዶዎች፤

መጽኡ ፪ኤሆሙ እንዘ ይትጋደሉ፣

ሁለቱም እየተጣሉ መጡ፤ እሊህ ሐማና መርዶክዮስ ናቸው፤

ወከነ ቃሎሙ ዓቢየ፤

ቃላቸውም እጅግ በዛ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወበቃለ ዚአሆሙ ተደለዉ አሕዛብ ለጸብእ።

በነዚያ ቃል አሕዛብ ለሰልፍ ተዘጋጁ፤

ከመ ይጽብእዎሙ ለሕዝብ ጻድቃን።

ጻድቃን እስራኤልን ይወጓቸው ዘንድ፤

፰፡ ወናሁ ዕለተ ጽልመት ወቆባር።

እነሆ ጭጋግ ጨለማ ናት ማለት መከራ የሚደረግባት ቀን ናት፤

ወሥቃይ።

መከራ የሚቻልባት ቀን ናት፤

ወምንዳቤ ወሕማም።

መከራ ጻዋትወ መከራ የሚደ ረግባት ቀን ናት፤

ወሁከት ዓቢይ ውስተ ምድር።

በዚህ ዓለም ዓቢይ ጽኑ ሁከት የሚደረግባት ቀን ናት፤

፱፡ ወተሐውኩ ጻድቃን።

ጻድቃን እስራኤል ታወኩ፤

ወኵሎሙ ሕዝብ ፈርሁ እምነ እኪቶሙ።

ከክፋታቸው የተነሣ ሕዝቡ ሁሉ ፈሩ፤

ወተደለዉ ለተኀጕሎ።

ለጥፋት ተዘጋጁ፤

፲፡ ወጸርሑ ኀበ እግዚአብሔር።

ወደ እግዚአብሔር ጮሁ፤

ወእምነ ጽራሆሙ ኮነ ንስቲት ነቅዕ።

ከጩኸታቸው የተነሣ አስቴር ተወለደች፤

ወእምዝ ውኅዘ ፈለግ ዓቢይ ዘብዙኅ ማዩ።

ተድላ ደስታው ብዙ የሆነ አርጤክስስ አስቴርን አገባት፤

፲፩፡ ወብርሃን ወፀሐይ ሠረቀ ላዕሌሆ።

እቴጌነት አደረሰላት፤

ወትሑታን ተለዓሉ።

የተዋረዱ እስራኤል ከፍ ከፍ አሉ፤

በልዕዎሙ ለክቡራን ፤

እስራኤል አሕዛብን አጠፏቸው፤

፲፪፡ ወተንሥአ መርዶክዮስ ርእዮ ዘንተ ሕልመ፡

መርዶክዮስ ይህን ሕልም አይቶ ተነሣ፡

ወአእመረ ከመ እግዚአብሔር ፈቀደ ይግበር፡

እግዚአብሔር ያደርገው ዘንድ እንደ ወደደ ዐወቀ፤

ወዐቀቦ ውስተ ልቡ።

በልቡናው፣ አስተዋለው ፤

ወፈቀደ ያእምር ኵሎ ነገሮ በሌሊት፡

ሌሊት ነገሩን ሁሉ ሊያውቅ ወደደ፤



፲፫፡ ወነበረ መርዶክዮስ ውስተ ዓፀድ ምስለ ገቦታ ወታራ ፪ቱ ሕፅዋኒሁ ለንጉሥ እለ የዓቅቡ ሀገረ።

መርዶክዮስ ሀገሩን ከሚጠብቁ ለንጉሡ ባለሟሎች ከሚሆኑ ከታራ ከገቦታ ጋራ በቤተ መንግሥት ተቀመጠ፤

፲፬፡ ወሰምዐ ምክሮሙ ዘይሔልዩ፡

ያሰቡትን ምክራቸውን ሰማ፤

ወአእመረ ወጠየቀ ከመ አስተ ዳለዉ ማዕሌተ።

ይቅትልዎ ለአርጤክስስ ንጉሥ፡

ንጉሡ አርጤክስስን በጫማው መርዝ ጨምረን ሰፍተን እንግ ደለው ብለው እንደ መከሩ አወቀ፤ ተረዳ፤ አንድም በሀገራቸውስ ልብ አልባና ጫማ አንድ ሁኖ ነው የሚሰፋ በውስጡ ዕባብ አድርገን እንግደለው ብለው መከሩ፡

ወነገሮ ለንጉሥ በእንቲአሆሙ፡

የነዚያን ነገር ለንጉሡ ነገረው፡

እሱ ነግሮት አይደለም፡ መርዶ ክዮስ ለአስቴር፣ አስቴር ለንጉሡ ነግራዋለች፤

፲፭፡ ወሐተቶሙ ንጉሥ ለክልኤሆሙ ሕፅዋኒሁ።

ንጉሥ ሁለቱ ባለሟሎቹን መረ መራቸው፡

ወአምኑ፡

አምን አሉ፡

ወተኰነኑ፡

ተቀጡ፤

፲፮፡ ወጸሐፎ ንጉሥ ለዝንቱ ነገር ውስተ ተዝካረ ዋቢያት፡

ንጉሡም የነገሥታቱ ወግ፣ ታሪክ በተጻፈበት በመጽሐፈ ነገሥት ጽፎ አኖረው፤

ወመርዶክዮስኒ ጸሐፎ ለዝንቱ ነገር፡

መርዶክዮስም ይህን ነገር ጻፈው፤

፲፯፡ ወአዘዞ ንጉሥ ለመርዶክዮስ ይፀመድ ውስተ ዓውድ።

ንጉሥ መርዶክዮስ እንደ ጸበል ረጭ ሁኖ በቤተ መንግሥት ይኖር ዘንድ አዘዘው፤

ወፈተዎ እንበይነ ዝንቱ።

ስለዚህ ነገር ድርጎ ዳረገው፤

፲፰፡ ሐማስ ዘአምዶቱ ብጋያዊ፡

የሀገር ስም ነው፡ አንድም ዘተዘምዶቱ አጋጋዊ፡ የአጋግ ወገን የሚሆን ሐማ ግን፤

ክቡር ውእቱ፡

ክቡር ነበረ፤

ወይቀውም ቅድመ ንጉሥ፡

በንጉሡ ፊት ይቆም ነበር፤

ወይፈቅድ ይግበር እኪተ ላዕለ መርዶክዮስ፡

በመርዶክዮስ ላይ ክፉ ነገር ያደርግ ዘንድ ይወድ ነበር፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሳዕለ ሕዝቡ በእንተ እልክቱ ፯ቱ ሕፅዋኒሁ ለንጉሥ፡

የንጉሡ ባለሟሎች ስለሚሆኑ ስለ ታሪ፣ ስለ ገቦታ በወገኖቹም ላይ ክፉ ነገር ሊያደርግ ይወድ ነበር ዘመዶቹ ነበሩና፡ አንድም በምክሩ ነበረበትና።

## ምዕራፍ ፪

፩፡ ወእምድኅረዝ ነገር በመዋዕሊሁ ለአርጤክስስ ንጉሥ፣

ከዚህም በኋላ በአርጤክስስ ዘመን፡

ውእቱ አርጤክስስ ዘነግሠ ላዕለ ፻፳ወ፯ቱ በሐውርት፡

ይህም አርጤክስስ በመቶ ሃያ ሰባት አህጉር የነገሠ ነው፡

እምብሔረ ሕንደኬ፣

ከሕንደኬ ጀምሮ በመቶ ሀያ ሰባት አህጉር የነገሠ ንጉሥ ነው፡

፪፡ ወበዉእቱ መዋዕል አመ ነግሠ በሱሳ ሀገር በሣልስ ዓመት እምዘ ነግሠ፣

በዚያ ወራት ሱሳ በሚባል ሀገር በነገሠ ጊዜ፣ በነገሠ በሶስተኛው ዘመን፡

ገብረ በዓለ ለአዕርክቲሁ፣

ወእምድኅረዝ ያለውን አመ ጣው፡ ለወዳጆቹ በአዳራሽ ተገኘላቸው፡

፫፡ ወለእለ ተርፉ አሕዛብ፣

ለቀሩትም አሕዛብ፡

ለፋርስ ወሜዶን፡

ለፋርስ ለሜዶን ሰዎች፡

ወለክቡራኒሆሙ፣

ለክቡሩ መኳንንቱ ፡

ወለመላእክተ ሠራዊት፣

ለሠራዊቱ አለቆች፡ በአዳራሽ ተገኘ፡

፬፡ ወእምድኅረ አርአዮሙ ብዕለ መንግሥቱ ወክብረ ትፍሥሕቱ በ፻ትወ፹ ዕለት፣

በመቶ ሰማንያ ቀን ፍጹም ጌትነቱን ካሳያቸው በኋላ፡

፭፡ ወሶበ ተፈጸመ መዋዕለ መርዓ፣

በዓል የሚደረግበት ቀን ከተፈ ጸመ በኋላ፡

ገብረ ንጉሥ በዓለ ዳግመ ለአሕዛብ እለ ተርፉ ውስተ ሀገር ወዓፀደ ንጉሥ፣

በቤተ ንጉሥ በከተማ ለቀሩ ንጉሥ በዓል አደረገ፡

ሰዱስ ዕለተ፣

ስድስቱን ቀን በከተማ ላሉ፡

ወሰኑየ ዕለተ፣

ሁለቱን ቀን ለቋሚ፣ ለለኋሚ በአዳራሽ ተገኘ፡

፮፡ ወሥርግው በሚላት፣

ቤቱ በነጭ ሐር ተጐዝጕዞ ነበር፡



ወበሀጌ ንጹሕ፣

የጌጥ ልብስ ለብሶ ነበር፡

ወዕውድ በሚላት ውስተ አሕባለ ቢሶስ በሕልቀተ ወርቅ ወብሩር ላዕለ አዕማደ ዕብን ዘጽርንሶ፣

ጽርንሶ በሚባል ዕንቊ አዕማድ (ምሰሶዎች) ላይ በሐር ገመድ በወርቅ ቀለበት የተያዘ ነጭ ሐር ዙሪያውን ተጋርዶ ነበር፡

ወዐራታት ዘወርቅ ወዘብሩር፣

የወርቅ የብር የሚሆኑ ዙፋኖች ተዘርግተው ነበር፡

ወጽፍጹፍ በዕብን ዘኅብረ መረግድ፣

መረግድ የሚባል ዕንቊ ተነጥፎበታል፡

ወበዕንቈ ጼኒና ወበዕብነ ጺርኑ፣

ጺርኑ ጼኒና የሚባል ዕንቊ ተነጥፎበታል፡

ወጥቀ ሠናይ ጸፍጸፉ ዘዘሊአሁ ኅብረ አስሩ፣

ልዩ ልዩ የሚሆን መልኩ ብዙ የሆነ ዕንቊ የተነጠፈበት አዳራሹ እጅግ ያማረ ነው፡

ወእንተ አውዱ ጽጌ ረዳ ሥሩዕ፣

በመጋረጃውም ዙርያ ጽጌ ረዳ ተነስንሶበታል፡

፯፡ ወጽዋዑኒ ዘወርቅ ወዘብሩር፣

የወርቅ የብር የሚሆን ዕዋውም፡

ወዘዕንቊ እንተ ረቂናን ወዘኪል ቅያን፣

የኪልቅያን የረቂናን ዕንቊ ያለበት ጽዋው፡

ድልው በሐሳበ ሠለስቱ እልፍ መካልይት፣

ሚዛኑ ሶስት እልፍ መክሊት ይሆናል፡

ወወይኑ ብዙኅ፣

ወይኑም ብዙ ነው ማለት መናኛውን ሠራዊቱ ይጠጣሉ፡

ወሠናይ መዓዛሁ ዘይሰቲ ንጉሥ፡

ንጉሡ የሚጠጣው መዓዛው ያማረ ነው ማለት ማለፊያውን እሱ ይጠጣል፡

፰፡ ወበዓሉሰ አኮ በሕገ ቀዳሚ ዘገብረ፣

በዓሉን ግን እንደአባቶቹ ያደረገ አይደለም፡

አላ በከመ ፈቀደ ውእቱ ንጉሥ፣

እሱ እንደወደደ አደረገ እንጂ፡

ወአዘዞሙ ለመገብቱ ይግበሩ ፈቃደ ዘዚአሁ ወፈቃደ ሰብእ፡

የሱን፣ የሰውንም ፈቃድ ይፈ ጽሙ ዘንድ ሹማምንቱን አዘዛ ቸው፡

፱፡ ወአስጢን ንግሥት ገብረት በዓለ ለአንስት እለ ውስተ ቤተ መንግሥታ እምነበ አርጤክስስ ንጉሥ፣

ንግሥት አስጢንም ከንጉሡ አስፈቅዳ ከቤተመንግሥቷ ላሉ ሴቶች ምሳ አደረገች፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ ወበሳብዕት ዕለት ሶበ ተፈሥሐ ንጉሥ ይቤሎ ለሐማ፤

በሰባተኛዪቱ ቀን ደስ ባለው ጊዜ ንጉሥ ሐማን እንዲህ አለው፡

ወለባዛን ወለታራ ወለቡላዚ ወለዘ ተወልታ ወለዘአባጠ ወለታባ ፯ቱ ሕፅዋኒሁ ለንጉሥ እለ ይት ለአክዎ፤

የሚያገለግሉት ባለሟሎቹን የንጉሥ ባለሟሎች የሚሆኑ ሰባቱን እንዲህ አላቸው፡

፲፩፡ ከመ ያምጽእዋ ለንግሥት ወያንግሥዋ፤

አምጥተው ያነግሷት ዘንድ አምጧት አለ፤ ስለምን ቢሉ መልከ መልካም ነበረችና መልኳን ለማሳየት ፤ አንድም እቴጌነት አላደረሰላትም ነበርና እቴጌነት ለማድረስ፤

ወያሠርግውዋ አክሊለ፤

ዘውድ ይደፉላት ዘንድ፤

ወያርእይዋ ለኵሉ መላእክተ አሕዛብ ስና፤

ለአሕዛብ አለቆች መልኳን ለማሳየት፤

እስመ ሠናይት ይእቲ፤

መልከ መልካም ነበረችና፤

፲፪፡ ወአበየት ሰሚአቶ አስጢን ንግሥት፡

አስጢን ንግሥት መስማቱን እምቢ አለች፤

ወኢፈቀደት ትምጻእ ምስለ ሕፅዋኒሁ፤

ከባለሟሎቹ ጋራ ትመጣ ዘንድ አልወደደችም፡

ተከዘ ንጉሥ ወተምዐ፤

ንጉሡ አዘነ ተቆጣ፡

፲፫፡ ወነገሮሙ ለአዕርክቲሁ በከመ ትቤ አስጢን፤

አስጢን የተናገረችውን ነገር ለወዳጆቹ ነገራቸው፤

ወይቤሎሙ ግበሩ እንከሰ ሕጎ ወኰነኔሁ፤

ከእንግዲህስ ሥርዓቱን፤ ፍርዱን አድርጉልኝ፡

፲፬፡ ወመጽኡ ኀቤሁ አርቄስዮስ ወርስቂስ ወማሌስየል ወመላእክቲሁ ለፋርስ ወሜዶን እለ ቅሩባን ኀበ ንጉሥ፤

ወደንጉሥ የሚቀርቡ የፋርስ የሜዶን አለቆች እኒህ ሁሉ ወደሱ መጡ፤

እለ ይነብሩ እቱተ ምስለ ንጉሥ፤

ከንጉሥ ጋራ ቆይታ የሚቀመጡ ወደሱ ቀረቡ፤

፲፭፡ ወነገርዎ ለንጉሥ ሕጎሙ ዘከመ ይሬስይዋ ለአስጢን ንግሥት፤

አስጢንን እንደምንም እንዲያደርጓት ሥራታቸውን ለንጉሡ ነገሩት፤



እስመ ኢገብረት በከመ አዘዞሙ ለሕፅዋን፡

ባለማሎቹን እንዳዘዛቸው አላደረገችምና፤

፲፮፡ ወይቤሎሙ አኪዎስ ለንጉሥ ወለመላእክቲሁ፤

አኪዎስ ንጉሡንና አለቆችን እንዲህ አላቸው፡

አኮ ላዕለ ንጉሥ ባሕቲቱ ዘአበሰት አስጢን ንግሥት፤

ንግሥት አስጢን የበደለች ንጉሡን ብቻ አይደለም፡

አላ ላዕለ ኵሉ መላእክት ወላዕለ መገብተ ንጉሥ፤

በንጉሡ ሹማምንት ባለቆችም ላይ ነው እንጅ፡

፲፯፡ ወነገርዎሙ ቃላ ለንግሥት ዘከመ ዐበየቶ ለንጉሥ፤

ንጉሡን እምቢ እንዳለችው የንግሥት ቃሏን ነገራቸው፡

ወሶበ ዛቲ ዮም ዐበየቶ ለንጉሥ አርጤክስስ፡

ይህች አስጢን ንጉሡን እምቢ ያለችው፤

፲፰፡ ከማሁ አንስትዮሙ ለመኳንንተ ፋርስ ወሜዶን ሰሚዖን ኵሎ ዘከመ ተዋሥአቶ ለንጉሥ፡

በፋርስ ያሉ የሜዶን መኳንንት ሚስቶች ንጉሡን እምቢ እንዳለችው ከሰሙ፤

ከማሁ ይትኀበላ እማንቱኒ አምታቲሆን፤

እነዚያም ባሎቻቸውን ይደፋፈራሉ፡

ወያስተሐቅራ፤

ይንቃሉ፤ ያቃልላሉ፡

፲፱፡ ወእመሰ ፈቀደ ንጉሥ የአዝዝ ለቤተ መንግሥቱ ለዝንቱ ሕገ ፋርስ ወሜዶን፤

ንጉሥ ሊያዝ቗ ቢወድ በቤተ መንግሥቱ ይዘዝ፤ አንድም ከወደደ የፋርስ የሜዶን ሥርዓት የሚሆን ይህንን ይጽፉት ዘንድ ይዘዝ፤ አንድም ለፋርስ ለሜዶን ሰዎች ይጻፉት፡

ወከመዝ ይግበርዋ ለይእቲ ኢትባእ እንከ ኀቤሁ፤

ወደሱ እንዳትገባ ይህችን ይሻሯት፤

ወመንግሥታኒ የሀብ ንጉሥ ለካልእት ብእሲት እንተ ትኄይሳ፡

ንግሥትነቷንም ከሷ ለምትበልጥ ለሌላ ይስጥ፡

፳፡ ወይስምዕዎ ለዝንቱ ሕግ ዘገብረ ንጉሥ በመንግሥቱ፤

ንጉሥ በመንግሥቱ የሠራውን ሥርዓት ይስሙት፡

ወእምዝ ኵሎን አንስት ያከብራ አምታቲሆን ባዕለኒ ወነዳየኒ፤

ከዚህ በኋላ ድኀም ባለጸጋም ቢሆን ሴቶች ባሎቻቸውን ያከብራሉ፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፡ ወዐደሞ ለንጉሥ ዝንቱ ነገር ወለመላእክቲሁ፣

ይህ ነገር ንጉሥንና አለቆቹንም ደስ አሰኛቸው፡

ወገብረ ንጉሥ በከመ ይቤ ምኪዎስ፣

ንጉሥም ምኪዎስ እንደ መከረው አደረገ፡

፳፪፡ ወለዐከ ንጉሥ ውስተ ኵሉ መንግሥቱ ለለበሐውርቲሆሙ፡

ንጉሥ በሚገዛው ሀገር ሁሉ በየሀገራቸው ላከ፡

በከመ ዝንቱ ቃል ከመ ይፍርሃሆሙ አንስትያሆሙ ውስተ አብያቲሆሙ፣

ንጉሡ እንደ ተናገረ ሴቶች በየቤታቸው ባሎቻቸውን ይፈሩ ዘንድ።

## ምዕራፍ ፪

### ጉባዔ

፩፡ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ረስዓ ንጉሥ፣

ከዚህ በኋላ ረሳት፡

ወኢተዘከራ እንከ ለአስጢን፣

ከዚያ ወዲያ አስጢንን አላሰባትም፡

እስመ ይዜክር ላቲ ዘከመ ተዋሥአቶ፣

እምቢ እንዳለችው ያስባታልና፡

፪፡ ወእምድኅረ ኩነና ይቤልዎ ደቂቁ ለንጉሥ፡

ከፈረደባት በኋላ የንጉሡ ብላቴኖች እንዲህ አሉት፡

ይኅሥሡ ሎቱ ለንጉሥ ደናግለ አዋልደ እለ ሠናይ ራእዮን፣

መልካቸው ያማሩ ቆንጆዎች ይፈለጉለት አሉ፡

፫፡ ወየአዝዝ ንጉሥ ውስተ በሐውርተ መንግሥቱ መላእክተ ወመሳፍንተ፡

ንጉሥ በሚገዛው ሀገር መኳንንቱን፣ መሳፍንቱን ይዘዝ፡

ወይኅረዩ ሎቱ አዋልደ ደናግለ እለ ሠናይ ራእዮን ውስተ ሀገረ ሱሳ፡

መልከ መልካም ያማሩ ቆንጆ ዎችን ሱሳ ከሚባል ሀገር ይምረጡለት፡

ወያብእዎን ውስተ አብያተ አንስት፣

ሴቶች ወደአሉበት ቤት ያግቧቸው፡

ወያውፍይዎን ለሕጽዋነ ንጉሥ፡

ለንጉሥ ባለሟሎች ይስጧቸው፡

ወየሀብዎን ትብዖን ወኵሎን መፍቅዶን፡

የሚቀቡትን ዘይቱን የሚፈልጉትን ሁሉ ይስጧቸው፡



፬፡ ወእንተ አደመቶ ለንጉሥ እምኔሆን ብእሲቱ ይእቲ ትንግሥት ምስሌሁ ህየንተ አስጢን፣

ከነዚህ ንጉሡን ደስ ያሰኘችው ስለ አስጢን ፈንታ ከሱ ጋራ ትነግሥ ዘንድ ሚስቱ ይህች ናት፡

ወአደሞ ለንጉሥ ዝንቱ ነገር፣

ይህ ነገር ንጉሥን ደስ አሰኘው፡

ወገብረ ከማሁ፣

እንዲሁ አደረገ፡

፭፡ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ውስተ ሱሳ ሀገር፣

ሱሳ በሚባል ሀገር አንድ ሰው ነበር፡

ዘስሙ መርዶክዮስ ወልደ ኢያኤሩ፣

የኢያኤሩ ልጅ ስሙ መርዶ ክዮስ የሚባል፡

ዘሴምዩ፣

ኢያኤሩን የሴምዩ ልጅ አለው፡

ዘእምነገደ ብንያም፣

ከነገደ ብንያም የተወለደ፡

፮፡ ዘተፄወወ እምኢየሩሌም፡

ከኢየሩሳሌም ተማርኮ የሄደ፡

ዘፄወዎ ናቡከደነፆር ንጉሠ ባቢሎን፡

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የማረከው መርዶክዮስ የሚባል አንድ ሰው ነበር፡ ነገር ሠሪ፣ ለማለት ሁለተኛ ደገመው፡ አነሣው፡

፯፡ ወቦቱ ወለት እንተ ሐፀና፡

ያሳደጋት ልጅ ነበረችው፡

ወለተ አሚናዳብ እኁሁ ለአቡሁ ዘስማ አስቴር፡

ስሟ አስቴር የምትባል ያባቱ ወንድም የአሚናዳብ ልጅ ፡

ወእምድኅረ ወጽአት እምአዝማዲሃ፣

አባት እናቷ ከሞቱ በኋላ፡

ወሐፀና ሎቱ ትኩኖ ወለተ፡

ልጅ ትሆነው ዘንድ አሳድጓት ነበር፡ አንድም ትኩኖ ብእሲተ ሚስት ትሆነው ዘንድ ይላል፡ እንደዛሬው ሥርዐት አልጸናም፡

ወይእቲ ወለት ዘሠናይ ራእያ፡

ይህችም ልጅ መልኳ ያማረ ነበር፡

፰፡ ወሶበ አዘዞ ንጉሥ አስተጋብኦ ሎቱ ብዙኃተ አዋልደ ውስተ ሱሳ ሀገር ኀበ ጋይ፡

ንጉሥ ባዘዘ ጊዜ ብዙ ልጆች ሱሳ በሚባል ሀገር ከጋይ ዘንድ ሰበሰቡለት፡

ወአምጽእዋ ለአስቴር ኀበ ጋይ አቃቤ አንስት፡

አስቴርን ሴቶችን ወደሚጠብቅ ጋይ አመጧት፡

፱፡ ወአደመቶ ይእቲ ወለት፡

ይህች ልጅ ደስ አሰኘችው፡

www.ethiopianorthodox.org

ወረከበት ሞገሰ በቅድሜሁ፤

በፊቱ ባለሟልነትን አገኘች፤

ወአፍጠነ ውሂቦታ ቅብዐ መክፈልታ፤

ፈንታዋን ዘይት ሰጣት፤ አንድም ውሂቦታ ቅብዓ ዘይት ፈጥኖ ሰጣት፤

ወመክፈልታ፤

ተረፉን፤

ወሰብኡ አዋልድ እለ ይትለአካሃ እምቤተ ንጉሥ፤

በንጉሥ ቤት የሚአገለግሏት ሰባት ልጆች ነበሯት፤

ወሠናየ ዐቀባሃ እለ ሐፀናሃ በውስተ ቤተ አንስት፤

በሴቶች ቤት የሚያሳድጓት ሰዎች አቀማጥለው አሳደጓት፤

፲፡ ወኢነገረት አስቴር አዝማዲሃ ወኢብሔራ፤

አስቴር እናት አባቷን፣ ሀገሯ ንም አልተናገረችም፤

እስመ መርዶክዮስ አዘዘ ኢታይድዕ፤

መርዶክዮስ እዳትናገር አዝዟ ታልና፤

፲፩፡ ወኵሎ አሚረ ይመጽእ መርዶ ክዮስ ኀበ አፀደ አንስት፤

መርዶክዮስ ሁልጊዜ ሴቶች ወደ አሉበት ቦታ ይመጣ ነበር፤

ከመ ይስማዕ ዜናሃ ለአስቴር ዘከመ ሀለወት፤

እንደምን እንዳለች የአስቴርን ዜና ይሰማ ዘንድ፤

፲፪፡ ወአመ በጽሐ ጊዜሆን ለእላ አዋልድ ከመ ይባእ ኀበ ንጉሥ፤

ወደንጉሥ ይገቡ ዘንድ የእኒህ ሴቶች ልጆች ጊዜያቸው በደረሰ ጊዜ፤

፲፫፡ ወሶበ ተፈጸመ፲ቱ ወ፪ቱ አውራኅ፤

ዐስራ ሁለቱ ወር በተፈጸመ ጊዜ

እስመ መጠነዝ መዋዕል ይነብሩ እንዘ ይትሔረሳ ወይሜነያ፤

ይህን ያህል ዘመን እየተንከባ ከቧቸው እየአስጌጧቸው ይኖ ራሉና፤

፮ቱ አውራኃ እንዘ ይትቀብዓ ቅብዓ ዕፍረት፤

ስድስት ወር የላዩን ገላ የሚ አጠራ ሽቱ እየቀቡ፤

ወ፮ቱ አውራኃ በአፈዋት፤

ስድስት ወር የውስጡን ገላ የሚያጠራ እያጠጡ፤

ወበቅብዓ አንስት ፤

ሴቶች የሚቀቡትን እየተቀቡ ይህን ያህል ዘመን ይቀመ ጣሉና፤



፲፬፡ ወእምዝ እንከ ይእቲ አሚረ፤

ከዚህም በኋላ ቀኑ በደረሰ ጊዜ፤

ይበውእ ኀበ ንጉሥ፤

ወደንጉሡ ይገባሉ፤

ወእንተ ውእቱ ፈቀደ ያመጽኡ ሎቱ እምቤተ አንስት፤

እሱ የወደደውን ሴቶች ከአሉበት ያመጡለታል፤

፲፭፡ ወፍና ሠርክ ትበውእ፤

ሲመሽ ትገባለች፤

ወጸቢሐ ትገብእ ቤተ አንስት ኀበ ጋይ ሕፅወ ንጉሥ ዓቃቤ አንስት፤

በነጋ ጊዜ ሴቶችን የሚጠብቅ የንጉሥ ባለሟል የሚሆን ጋይ ወደአለበት ወደ ሴቶች ቤት ትመለሳለች፤

ወኢትደግም እንከ በዊአ ወገቢአ ኀበ ንጉሥ፤

ዳግመኛ ወደንጉሥ አትወጣም አትገባም፤

ለእመ ለሊሁ ኢጸውዓ፤

እሱ ካልጠራት፤

፲፮፡ ወአመ በጽሐ ዕለተ ዕብሬታ ለአስቴር ወለተ አሚናዳብ እኁወ አቡሁ ለመርዶክዮስ፤

የመርዶክዮስ የአባቱ ወንድም የአሚናዳብ ልጅ የአስቴር ተራ በደረሰ ጊዜ፤

ከመ ትባእ ኀበ ንጉሥ ገብረት በከመ አዘዛ ሕፅው ዓቃቤ አንስት፤

ወደንጉሥ ትገባ ዘንድ ሴቶችን የሚጠብቅ የንጉሥ ባለሟል እንደ አዘዛት አደረገች፤

እስመ ባቲ ሞገስ ለአስቴር በኀበ ኵሉ ዘይሬእያ፤

በሚያይዋት ሰዎች ዘንድ ለአስቴር መወደድ ነበራትና፤

፲፯፡ ወቦአት አስቴር ኀበ ንጉሥ አርጤክስስ በ፲ቱወ ፪ቱ አውራኀ በወርኀ አዳር በሳብዕ ዓመት ዘመንግሥቱ፤

በነገሠ በሰባት ዓመት፤ በዐሥራ ሁለተኛው ወር በመጋቢት አስቴር ወደ አርጤክስስ ገባች፤

፲፰፡ ወአደመቶ አስቴር ለንጉሥ፤

አስቴር ንጉሡን ደስ አሰኘችው፤

ወረከበት ሞገሰ ፈድፋደ እምኵሎን ደናግል፤

ከሴቶች ሁሉ ይልቅ ፈጽማ ባለሟልነትን አገኘች፤

ወአሠርገዋ አክሊለ አንስት፤

እቴጌነት አደረሰላት፤

፲፱፡ ወገብረ ንጉሥ በዓለ ለኵሉ፤ አዕርክቲሁ ወለሠራዊቱ ሰቡዓ መዋዕለ፤

ንጉሥ ለወደዳቸው ለሠራዊቱ ሰባት ቀን ምሳ አደረገ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአዕበዮ ለመርዓ አስቴር፣

የአስቴርን ሠርግ አበዛው፣ አከበረው፤ ለነዚያ ሁለት ቀን ሦስት ቀን ሠርግ ሲያደርግ ለእሷ ሰባት ቀን አድርጎ ላታልና፤

ወገብረ ኅዳጋቲሃ ኵሎ ደወለ መንግሥቱ፣

በሚገዛው አገር ጉልት ሰጣት፤

፳፤ ወመርዶክዮስሰ ይፀመድ በውስተ ዓፀዱ፣

መርዶክዮስ ግን በሷ ምክንያት እንደ ጠበል ረጭ ሁኖ ያገለግል ነበር፤

፳፩፤ ወአስቴርኒ ኢያይድአት ብሔራ፣

አስቴር አገሯን አልተናገረችም፤

እስመ ከማሁ አዘዘ መርዶክዮስ ከመ ትፍራሀ እግዚአብሔርሃ፣

እግዚአብሔርን ትፈራ ዘንድ ጣዖት እንዳታመልክ መርዶክዮስ ነግሯት ነበርና፤

ወትግበር ትእዛዞ በከመ ሀለወት ምስሌሁ፣

ከሱ ጋራ ታደርገው እንደ ነበረች ትእዛዙን ታደርግ ዘንድ፤

ወአስቴርሰ ኢሐደገት ሕጋ፣

አስቴር ግን ሥርዓቷን አልተወችም፤

፳፪፤ ወተከዙ ፪ቱ ሕፅዋኒሁ ለንጉሥ ሊቃነ ዓቀብተ ርእሱ፣

ንጉሡን የሚጠብቁ ሰዎች አለቆች ባለሟሎቹ አዘኑ፤

እስመ ዓብየ መርዶክዮስ፣

መርዶክዮስ ከብሯልና፤

ወፈቀዱ ይቅትልዎ ለንጉሥ፣

በመርዶክዮስ ቀንተው ንጉሡን ሊገድሉት ወደዱ፤ አንድም በሀገራቸው ልብ አልባና ጫማ አንድነት ነው የሚሰፋ፤ በውስጡ ዕባብ አድርገን እንስጠው ብለዋልና፤

፳፫፤ ወሰምዐ መርዶክዮስ ወነገራ ለአስቴር፣

መርዶክዮስ ሰምቶ ለአስቴር ነገራት፤

ወይእቲኒ አይድአቶ ለንጉሥ ምክሮሙ፣

አስቴርም ለንጉሥ ምክራቸውን ነገረችው፤

፳፬፤ ወሰቤሃ ሐተቶሙ ንጉሥ ለእልክቱ ፪ቱ ሕጽዋን፣

ያን ጊዜ ንጉሥ ሁለቱን ባለሟሎቹን መረመራቸው፤

ወአምኑ፣

አምን አሉ፤

ወእምዝ ሰቀሎሙ፣

ከዚህ በኋላ ሰቀላቸው፤



ወአዘዘ ንጉሥ ይጽሐፍዎ ለዝንቱ ውስተ መጽሐፈ ኖብዖተ ነገሥት ለተዝካር በእንተ አኩቴቱ ለመርዶክዮስ፣

መርዶክዮስን ስለ ማክበር መታሰቢያ ሊሆን የነገሥታቱ ወግ ታሪክ በተጻፈበት ታሪክ ነገሥት ይጽፉት ዘንድ አዘዘ።

## ምዕራፍ ፬

፩፤ ወእምድኅረ ዝንቱ አዕበዮ ንጉሥ አርጤክስስ ለሐማ ዘአምዱቱ ብግያዊ፣

አርጤክስስ ከሱ በኋላ የአምዱቱ ልጅ የብግያ ሰው ፤ አንድም ዘተዘምዱቱ አጋጋዊ ይላል ትውልዱ ከአጋግ ወገን የሚሆን ሐማን አከበረው፣ አገነነው፤

ወአንበሮ ላዕለ እምነ ኵሉ አዕርክቲሁ፣

ከባልንጀሮቹ ሁሉ በላይ አስቀመጠው፤

፪፤ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ እለ ውስተ ዓፀዱ፣

በቤተ መንግሥት ያሉ ሁሉ ሰገዱለት፤

እስመ ከማሁ ይግበሩ አዘዘ ንጉሥ፣

ንጉሥ ይሰግዱለት ዘንድ አዝዟልና፤

ወመርዶክዮስሰ ባሕቲቱ ኢይሰግድ ሎቱ፣

መርዶክዮስ ግን አልሰገደለትም፤ አሪት ዘሰገደ ለፍጡር ርጉም ውእቱ ትላለችና፤

፫፤ ወይቤልዎ እለ ውስተ ቤተ ዓፀደ ንጉሥ፣

በቤተ መንግሥት ያሉ ሰዎች እንዲህ አሉት፤

አንተ መርዶክዮስ ለምንት ኢትትኤዘዝ ለቃለ ንጉሥ፣

አንተ መርዶክዮስ ለንጉሥ የማትታዘዝ ለምድነው አሉት፤

፬፤ ወኵሎ አሚረ ይቤልዎ ከመዝ፣

ሁልጊዜ እንዲህ ይሉታል፤

ወየአቢ ሰሚዖቶሙ፤

እሱም አይሆንም ይላቸው ነበር፤

ወነገርዎ ለሐማ ከመ የአቢ ትእዛዘ ንጉሥ፣

መርዶክዮስ የንጉሡን ትእዛዝ አልሰማም እንዳለ ለሐማ ነገሩት፤

ወነገርዎ ከመ አይሁዳዊ ውእቱ፣

አይሁዳዊ እንደሆነም ነገሩት፤

፭፤ ወሶበ አእመረ ሐማ ከመ ኢይሰግድ ሎቱ መርዶክዮስ ተምዐ ጥቀ፣

መርዶክዮስ እንዳልሰገደለት በሰማ ጊዜ ሐማ ፈጽሞ ተቆጣ፤

www.ethiopianorthodox.org

፮፡ ወፈቀደ ያጥፍኦሙ ለኵሎሙ አይሁድ እለ ደወለ መንግሥቱ ለአርጤክስስ ህለዉ።

አርጤክስስ በሚገዛው ሀገር አውራጃ ያሉ አይሁድን ሁሉ ያጠፋቸው ዘንድ ወደደ፤

፯፡ ወገብረ ከመዝ ፣ በ፲ቱወ፪ቱ ዓመት እምዘ ነግሠ አርጤክስስ፡

አርጤክስስ በነገሠ በዓሠራ ሁለት ዘመን እንዲህ ሆነ፤

አስተዓፀወ ዕለተ እምዕለት ወወርኃ እምወርኃ ከመ ያጥፍኦሙ ለዘመደ መርዶክዮስ በአሐቲ ዕለት።

የመርዶክዮስን ዘመዶች በአንድ ቀን ያጠፋቸው ዘንድ ከቀን ቀን ከወር ወር ቢያወጣጣ፤

ወወረደ ዕፁ ላዕለ ዐሡሩ ወረቡዑ ለሠርቀ ወርኃ አዳር።

ፈላስፋ ነበርና እስራኤል የሚጠፉበት በመጋቢት በአሥራ አራት ቀን እንደሆነ ተገለጸለት፤

፰፡ ወነገሮ ለአርጤክስስ ወይቤሎ።

ለአርጤክስስ ነገረው እንዲህ አለው፤

ሀሎ ሕዝብ ዐላዊ እምውስተ ኵሉ ሕዝበ መንግሥትከ።

በምትገዛቸው ሀገር ካሉ ወገኖች ወንጀለኛ ወገን አለ፤

ወሕጎሙኒ ካልዕ እምነ ኵሉ አሕዛብ።

ሕጋቸው ሥርዐታቸው ከአሕዛብ ሁሉ ልዩ ነው፤

ወኢይትኤዘዙ ለሕገ ንጉሥ።

ለንጉሥ ሥርዐት አይታዘዙም፤

ወኢርቱዕ ይኅድጎሙ ንጉሥ።

ንጉሥ ይተዋቸው ዘንድ አይገባም፤

፱፡ ወእመሰ ፈቀደ ንጉሥ የአዝዝ ያጥፍዕዎሙ።

ንጉሥ የምትወድስ ከሆነ ያጠፏቸው ዘንድ እዘዝ፤

ወናሁ አነ እጽሕፍ ወአበውእ ፲፻ መካልየ ብሩር በመዝገበ ንጉሥ።

እነሆ እኔ በንጉሥ ደብዳቤ ጽፌ እልፍ መክሊት ብር አገባለሁ፤

፲፡ ወአውጽአ ንጉሥ ሕልቀቶ ወመጠዎ ውስተ እዴሁ ለሐማ፤

ንጉሥ ቀለበቱን አውጥቶ ለሐማ በእጁ ሰጠው፤

ከመ ይሕትም ሰበ ጸሐፈ በእንተ አይሁድ።

የአይሁድን ነገር በጻፈ ጊዜ አርጤክስስ እንዲህ አለ ብሎ ያትም ዘንድ፤

፲፩፡ ወይቤሎ ንጉሥ ለሐማ።

ንጉሥ ሐማን እንዲህ አለው፤

ወርቅከኒ ይኩን ለከ።

ጠላት ብታጠፋልኝ ወርቅ እከፈልሃለሁን ወርቁ ላንተ ይሁን፤

ሕዝበኒ ግበር በከመ ፈቀድከ።

ሕዝቡን እንደወደድህ አጥፋ፤



፲፪፡ ወጸውአ ጸሐፍተ ንጉሥ በቀዳሚ ወርኀ አመ ዐሥሩ ወሠሉሱ ለሠርቅ።

ሚያዝያ በባተ በአሥራ ሦስት ቀን የንጉሡን ጸሐፊዎች ጠራ፤

ወጸሐፉ በከመ አዘዞሙ ሐማ ለመላእክት ወለመሳፍንት ዘኵሉ በሐውርተ ሕንደኬ እስከ ኢትዮጵያ ለ፻ወ፳ወ፯ቱ በሐውርት።

በሕንደኬ አውራጃ በአሉ ሁሉ ለሹማምንቱ አለቆች ሐማ እንደ አዘዛቸው እስከ ኢትዮጵያ ድረስ ለመቶ ሃያ ሰባት ሀገሮች ጻፉ፤

ለለምልክና አሕዛቢሆሙ።

በሚገዛው ሀገር ላሉ ሁሉ፤

በበነገረ በሐውርቲሆሙ በቃለ አርጤክስስ ንጉሥ።

አርጤክስስ እንዲህ አለ ብለው በየቋንቋቸው ጻፉ፤

፲፫፡ ወፈነወ ሐዋርያተ ውስተ ደወለ መንግሥቱ ለአርጤክስስ።

አርጤክስስ ወደሚገዛው አውራጃ መልክተኞችን ሰደደ፤

ያጥፍእዎሙ ለዘመደ አይሁድ በአሐቲ ዕለት በወርኃ አዳር አመ ዐሥሩ ወረቡዑ።

የአይሁድን ወገኖች በመጋቢት በዐሥራ አራተኛ ቀን በአንዲት ቀን ያጠፏቸው ዘንድ፤

ወይበርብርዎሙ ንዋዮሙ።

ገንዘባቸውን ይበዘብዟቸው ዘንድ፤

፲፬፡ ወከመዝ ይብላ መጻሕፍቲሁ ለንጉሥ አርጤክስስ ዓቢይ።

ገናና የሚሆን የንጉሥ አርጤክስስ ደብዳቤዎች እንዲህ ይላሉ፤

እምነ ሕንደኬ እስከ ኢትዮጵያ ለ፻ ወ፳ ወ፯ በሐውርት።

ከሕንደኬ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ለመቶ ሃያ ሰባት አህጉር፤

ለመላእክት ወለመሳፍንት ወለመኳንንት።

ላለቆቹ፣ ለመሳፍንቱ ለሹማምንቱ፤

ወለሥዩማን።

ለሹማምንቱ ለተወራጆቹ፤

ከመዝ ጸሐፈ።

እንዲህ ብሎ ጻፈ፤

፲፭፡ ብዙኃነ አሕዛበ ኮኒንየ።

ብዙ አሕዛብን ገዝቼ፤

ወኵሎ በሐውርተ አግረርየ።

ሀገሩን ገዝቼ፤

ፈቀድኩ።

አይሁድን አጠፋ ዘንድ ወደድኩ፤ አንድም ለሰው ሁሉ በጎ ነገር አደርግ ዘንድ ወደድኩ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአኮ በጽንዓ መንግሥትየ ዘአዓቢ ርእስየ፤

ራሴን የማከብር የማገን በጽንዓ መንግሥቴ አይደለም፡ አንድም የሚወዱኝን ሰዎች የማጠፋ አይደለሁም፡

አላ በጽምው ወበየውሃት ለዝሉፉ፤

ሁልጊዜ በየውሃት በጸጥታ ጸንቼ እኖራለሁ እንጂ፤ በጽምው ባለው በፀሐይም ይላል፤

አስተናቢርየ ኵሎ ዘሊተ ይትኤዘዝ ዘእንበለ ድንጋጼ ዝሞገደ ማዕበል፡

ሞገድ ፀጥ እንዲል ያለድንጋጤ የሚታዘዙልኝን ሁሉ አዘጋጅቼ፤

ሠሪዕየ ኵሎ በከመ መንግሥትየ ሥሩዕ ወህዱዕ፤

መንግሥቴ ጸጥ ያለ የተከናወነ እንደሆነ በፀጥታ በየውሃት እኖራለሁ እንጂ፤

፲፮፡ ወትብጻሕ እስከ አጽናፈ በሐውርት፤

እንዲህ የምትል ክታብ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ድረስ ትድረ ስላቸው፡

ወእሔድስ ሰላመ ዘእምነበ ኵሉ ሰብእ ይትፈቀር፤

ከሕዝቡ ሁሉ የተገኘ ፍቅርን አጸናለሁ፤

፲፯፡ አሀ ብሂልየ ለመማክርትየ፤

መካሮቼን እሺ በጎ ብዬ፤

በዛ እክል ሠሪዖቶ ለዝሉፉ ለዝንቱ፤

ይህን በእውነት ሠራርቶ ማኖር በሚቻለኝ ገንዘብ፡

መጻእኩ አሠኒ በልብዩ ዘእንበለ ንስሐ፤

ያለመፀፀት በልቡናዬ በጎ ነገር አደርግ ዘንድ መጣሁ፤

፲፰፡ ወበአማን ዘተልእከ በንጹሕ፤

በእውነት በንጹሕ ያገለገለ፡

ዘእምታሕቴየ ሐማ፤

ከኔ በታች ያለ ሐማ፡

መርሐነ፤

ወደነገሩ መራን፤

ወኢየይድአነ ከመ በኵሉ በሐውርት፤

በየሀገሩ ሁሉ፤

ወበኵሉ አሕዛብ ዘውስተ ኵሉ ዓለም፤

በዓለሙ ሁሉ አሕዛብ፤

ተደመረ ሕዝብ ዘእኩይ ሕጉ፤

ሥርዐቱ ክፉ የሆነ ሰው እንደ ተጨመረ ነገረን፤

ዘኢይትኤዘዝ ለትእዛዘ ንጉሥ ዘልፈ እምነ ኵሉ ሕዝብ፤

ከሕዝቡ ተለይቶ ለንጉሥ ትእዛዝ የማይታዘዝ፤



ወየአቢ በሥርዓተ ሕግነ፤

በኛ ሕግ፤ በኛ ሥርዓት ጸንቶ መኖርን እምቢ የሚል ወገን እንደተጨመረ ነገረን፤

፲፱፡ ወረከብናሁ ለዝንቱ ሕዝብ ፍሉጥ እንተ ባሕቲቱ ካልእ ሕጉ እምነ ኵሉ ሰብእ፤

ከሰው ሁሉ ሕጉ ለብቻው ልዩ የሚሆን ይህን ወገን አገኘነው፡

ወነኪር ወፍሉጥ ወውጹዕ እምሕገ ዚአነ፤

ከእኛ ሕግ የወጣ ፣ የተለወጠ ልዩ እንደሆነ አገኘነው፤

ወይገብሩ እኪተ ለግዕዘሙ፤

ለባሕርያቸው የሚስማማቸውን ክፉን ነገር ይሠራሉ፤

ወይሬስይዋ ለመንግሥትነ ከመ ወኢምንት፤

መንግሥታችንን እንደሌለች ያደርጓታል፤

፳፡ ወናሁ አዘዝነ በእንተ ዘጸሐፍነ ለክሙ በመጻሕፍቲሁ ለሐማ ዘተሠይመ ላዕለ ኵሉ ዘውእቱ እምታሕተ አቡነ፤

ይኸውም ከአባታችን በታች ያለ በሀገሩ ሁሉ የተሾመ በሐማ መጽሐፍ ስለ ተጻፈላችሁ እነሆ አዘዝነ፤

ከመ ያጥፍዕዎሙ ለኵሎሙ ምስለ አንስቲያሆሙ ወደቂቆሙ በመጥባሕተ ፀሮሙ፤

በጠላቶቻቸው ጦር ከሚስቶቻቸው ከልጆቻቸው ጋራ ሁሉንም ያጠፏቸው ዘንድ አዘዝነ፡

እንዘ ኢትምሕክዎሙ ወኢትምሕርዎሙ፤

ሳታዝኑላቸው ሳትራሩላቸው፤

አመ ሠርቀ ፲ወ፬ቱ ለወርኃ አዳር፤

መጋቢት በባተ በ፲ሥራ አራት ቀን፤

በ፲ቱ ወ፪ቱ ለወርኀ ዛቲ ዓመት፤

በዚች ዓመት ባሥራ ሁለተኛው ወር በመጋቢት፤

፳፩፡ ከመ ለንዑሰሙ ወለዐቢዮሙ ከመ ታውርድዎሙ ውስተ ሲኦል በአሐቲ ዕለት፤

ታላቁንም ታናሹንም ባንዲት ቀን ወደመቃብር ታወርዷቸው ዘንድ አዘዝነ፤

ወእልበ ዘታተርፉ እምኔሆሙ፤

ከነዚያ የምታስቀሩት የለም፤

ከመ ታዕርፍ እንከ በሐውርት እምነ ግብሮሙ ለዝሉፉ፤

ሀገራቱ ሁሉ ከክፉ ሥራቸው ታርፍ ዘንድ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፱፡ ወአርአዮሙ በለሀሳስ መጻሕፍቲሁ፡

መጻሕፍቱን በቆይታ አሳዩ ቸው፡

ወሢመ ውስተ በሐውርቲሆሙ፤

በየሀገራቸው ሁሉ አኖረ፤

ገባዔ፤

ወአዘዘ ለኵሉ አሕዛብ ከመ ይኩኑ ለውእቱ ዕለት፤

ለዚያ ቀን ይሆኑ ዘንድ አሕዛብን ሁሉ አዘዘ፤

፴፡ ወይጌግዩ በውስተ ሱሳኒ ይግበሩ ከማሁ፤

አሁን እንዳልናቸው ለማድረግ በሱሳ ያሉ ሁሉ ይቺኩሉ ዘንድ፡

ንጉሥስ ወሐማ ያፀምዑ፤

ንጉሡና ሐማ ግን ያዳምጡ ነበር፡

ወተሐውከት ኵላ ሀገር፤

ሀገሪቱ ሁሉ ታወከች፡፡

ምዕራፍ ፬

፩፡ ወሶበ አእመረ መርዶክዮስ ዘከመ ኮነ፤

መርዶክዮስ የሆነውን ነገር ባወቀ ጊዜ፤

ሠጠጠ አልባሲሁ ወለብሰ ሠቀ፤

ልብሱን ቀደደ፤ ማቅ ለበሰ፡

ወወደየ ሐመደ ዲበ ርእሱ፡

አመድ በራሱ ላይ ነሰነሰ፡

ወሮፀ እንተ መርኅበ ሀገር እንዘ ይጸርሕ በዓቢይ ቃል፤

ቃሉን አሰምቶ እየጮኸ ወደ አደባባይ ፈጥኖ ሄደ፤

ወይብል ትቀትሉኑ ሕዝበ እንበለ አበሳ፤

በደል የሌለበትን ሰው ታጠፋ ላችሁን እያለ፤

፪፡ ወበጽሐ ኀበ ኆኅተ ንጉሥ ወቆመ፤

ከንጉሡ በር ደርሶ ቆመ፤

እስመ ኢይከውኖ ለበዊዕ ውስተ ዓፀደ ንጉሥ እንዘ ሠቀ ይለብስ ወሐመድ ዲበ ርእሱ፤

ትቢያውን በራሱ ነስንሶ፤ ማቅ ለብሶ ወደ ንጉሥ መሄድ አይገባምና፤

፫፡ ወበኵሉ በሐውርት ኀበ ተፈነወ መጻሕፍት፤

ደብዳቤዎች በሔዱበት አገር ሁሉ፤

ጽራኅ ወብካይ ወዓቢይ ላሕ ለአይሁድ፤

ለአይሁድ ጩኸት፤ ልቅሶ ጽኑ ኃዘን ሆነ፤



ሠቀ ወሐመደ ነጸፉ ኵሎሙ አይሁድ፤

አይሁድ ሁሉ ማቅ ለብሰው አመድ ነስንሰው አዘኑ፤

፬፡ ወቦኡ ሕጽዋኒሃ ወአዋልዲሃ ለንግሥት፤

የንግሥት ባለሟሎቿ ልጆቿ ገቡ፡

ወአይድእዋ ለንግሥት፤

ለአስቴር ነገሯት፤

ደንገጸት ሶበ ሰምዐት ዘንተ ዘከመ ኮነ፤

ይህ እንደሆነ በሰማች ጊዜ ደነገጠች፤

ወፈነወት አልባሰ ለመርዶክዮስ ዘይለብስ፤

ለመርዶክዮስ የሚለብሰውን ልብስ ሰደደችለት፤

ወአበየ ኃዲገ ሠቀ፤

ማቁን መተው እምቢ አለ፤

፭፡ ወጸውአቶ አስቴር ለአክራትዮስ ሕፅው ዘይቀውም ቅድሜሃ፤

በፊቷ የሚቆም አክራትዮስን ጠራችው፤

ወለአከቶ ይስማዕ ጥዩቀ ነገረ በኀበ መርዶክዮስ፤

ከመርዶክዮስ ዘንድ እውነቱን ነገር ይሰማ ዘንድ ላከችው፤

፯፡ ወነገሮ መርዶክዮስ ዘከመ ኮነ፤

መርዶክዮስም የሆነውን ነገር ነገረው፤

ወዘከመ ይቤሎ ሐማ ለንጉሥ እልፈ መካልየ አበውእ ውስተ መዝገቡ ለንጉሥ፤

ሐማ ንጉሡን ወደ ንጉሥ መዝገብ እልፍ መክሊት አገባለሁ እንዳለ ነገረው፤

ከመ ይቅትሎሙ ለአይሁድ፤

አይሁድን ያጠፋቸው ዘንድ፤

፰፡ ወቃለ ነገሩ ለአንጻክቲ መጽሐፍ ዘአንበሩ ውስተ ሱሳ፤

በሱሳ ያኖራት የዚያችን መጽሐፍ የነገሩን ቃል ነገረው፤

ከመ ይቅትልዎሙ ለአይሁድ፤

አይሁድን ይገድሏቸው ዘንድ፤

፱፡ ወወሀቦ አርአያሃ ያርእያ ለአስቴር፤

ደብዳቤውን ለአስቴር ያሳያት ዘንድ ሰጠው፤

ወይቤሎ በላ ትባእ ኀበ ንጉሥ ትስአሎ ወታስተብቍዖ፤ በእንተ ሕዝባ፤

ስለ ወገኖቿ ትለምነው፤ ትማልደው ዘንድ ወደ ንጉሥ እንድ ትገባ ነገራት፤

ተዘከሪ መዋዕለ ምንዳቤኪ ዘከመ ተሐፀንኪ ውስተ እዴየ፤

የባሬውን ተድላ ደስታ አትዩ በኔ እጅ እንዳደግሽ ወሬት አስቢ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ሐማ ዘእምታሕተ ንጉሥ አዘዘ ይቅትለነ፣

ከንጉሥ በታች ያለ ሐማ ይገድለን ዘንድ አዝዟልና፤

ወሰአሊ ኀበ እግዚአብሔር እግዚእ፣

ወደ ጌታ ወደ እግዚአብሔር ለምኚ፤

ወንግሪዮ ለንጉሥ በእንቲአነ፣

የኛን ነገር ለንጉሥ ንገሪው፤

ወአድኅንነ እሞት፤

ከሞት አድኚን፤

፱፡ ወቦአ አክራትዮስ ወነገራ ለአስቴር ዘንተ ኵሎ ነገረ፣

አክራትዮስ ለአስቴር ይህን ሁሉ ነገራት፤

፲፡ ወትቤሎ አስቴር ለአክራትዮስ ሑር ኀበ መርዶክዮስ፣

አስቴር አክራትዮስን ወደመር ዶክዮስ ሂድ፤

ወበሎ ኵሉ አሕዛብ የአምራ ለዛቲ መንግሥት፣

ይህችን መንግሥት አሕዛብ ሁሉ ያውቋታል፤

ከመ ዘቦአ ኀበ ንጉሥ ውስተ ውሳጤ ዓፀድ እመኒ ብእሲ ወብእሲት ዘኢጸውእዎ፣

ያልጠሩት ሴትም ወንድም ቢሆን ወደልፍኝ ከንጉሡ ዘንድ የገባ፤

አልቦ ሕይወት፣

ሕይወት እንደሌለው ያውቋታል፤

እመ ኢለከፎ ንጉሥ በበትሩ እንተ ወርቅ፣

በወርቅ ዘንግ ንጉሥ ካልነካው፤

ዳዕሙ ውእቱ ዘየሐዩ፣

እሱ በበትሩ ቢነካው ይድናል እንጂ፤

ኪያየኒ ኢፀውዓኒ ከመ እባእ ኀበ ንጉሥ፣

እኔንም ወደንጉሥ እገባ ዘንድ አልጠራኝም፤

ሠለስ መዋዕል ዮም፣

ከጠራኝ ዛሬ ሦስተኛ ቀን ነው፤

፲፩፡ ወአይድዖ አክራትዮስ ለመርዶ ክዮስ ዘትቤሎ አስቴር፣

አክራትዮስ አስቴር የነገረ ችውን ለመርዶክዮስ ነገረው፤

፲፪፡ ወይቤሎ መርዶክዮስ ለአክራ ትዮስ፣

መርዶክዮስ አክራትዮስን እን ዲህ አለው፤

ሑር በላ ኢትበሊ አስቴር አሐቲ አነ ባሕቲትየ እምነ ኵሉ አይሁድ በበይነ መንግሥትየ፣

ሂደህ መንግሥቴ ከጸናች ከአይ ሁድ ተለይቼ አስቴር ብቻዬን እኖራለሁ አትበይ በላት፤



እመ ተጸመምኪ ዮምኬ፣

ዛሬ ቸል ብትዪ፤

ለአይሁድሂ እንተ ባዕድሂ ይሜውሮሙ፣

አይሁድን በሌላ ያድናቸዋል፤ አንድም እመ ተጸመምኪ፤ ዛሬ አንቺ ዝም ብትዪ አይሁ ድን በሌላ ያጠፋቸዋል፤

፲፫፡ ወኢያድኅኖሙ፣

አያድናቸውም፤

አንቲሰ ወቤተ አቡኪ፣

ትጠፍዑ ያለበት ነው፤ ያባትሽ ወገኖችና አንች ግን ትጠፋላችሁ፤

ወመኑ የአምሮ ዮጊ ለዝንቱ መዋዕለ ንግሥኪ፣

ወይስ የመንግሥትሽን ወራት ማን ያውቃል፤

፲፬፡ ወአግብአቶ አስቴር ለዝንቱ ዘመጽአ ኀቤሃ እምኀበ መርዶክዮስ፤

ከመርዶክዮስ ወደእሷ የመጣ ውን መልእክተኛ መልሳ ላከችው፤

እንዘ ትብል ሑር አስተጋብአሙ ለአይሁድ እለ ውስተ ሱሳ፣

በሱሳ ያሉ አይሁድን ሰብስ ባቸው ብላ ላከችው፤

ጹሙ ሊተ ኢትብልዑ ወኢትስተዩ፣

ለእኔ ብላችሁ ጹሙልኝ አትብሉ አትጠጡ፤

እስከ ሠሉስ ዕለት መዓልተ ወሌሊተ፣

እስከ ሦስት ቀን ድረስ በመዓልትም በሌሊትም ጹሙ አትብሉ፤

አነኒ ወአዋልድየ ንጸውም፤

እኔና ልጆቼም እንጾማለን፤

ወእምዝ እበውእ ውስተ ንጉሥ፣

ከዚህ በኋላ ወደ ንጉሥ እገባ ለሁ ፤

ወእመ አኮ እመውት፣

መዳኑም ባይሆን እሞታለሁ፤ አንድም ብሞትም ልሙት አለች፤

፲፭፡ ወሖረ መርዶክዮስ ወገብረ ኵሎ ዘአዘዘቶ አስቴር፣

መርዶክዮስ ሂዶ አስቴር ያዘዘችውን ሁሉ አደረገ፤

፲፮፡ ወሰዓለ ኀበ እግዚአብሔር እንዘ ይዜክር ኵሎ ዘገብረ እግዚ አብሔር፣

እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አስበ ወደ እግዚአብሔር ለመነ፤

፲፯፡ ወይቤ እግዚአብሔር እግዚእ ዘኵሎ ትመልክ፣

እንዲህ አለ፤ ሁሉንም የምትገዛ እግዚአብሔር፤

እስመ በሥልጣንከ ገበርከ ኵሎ፣

ሁሉን የፈጠርህ በሥልጣንህ ነውና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአልቦ ዘይትቃ ወመከ እመ ፈቀድከ ታድኅኖሙ ለእስራኤል፤

እስራኤልን ታድናቸው ዘንድ ብትወድ የሚቃወምህ የለም፡ አንድም የሚቃውምህ የሌለ፡

፲፰፡ ወአንተ ገበርከ ሰማየ ወምድረ፤

ሰማይን፤ ምድርን የፈጠርህ አንተ ነህ፡ አንድም የፈጠርህ አንተ፡

ወኵሎ መድምመ በታሕተ ሰማይ፤

ከሰማይ በታች ያለውን ሁሉ የፈጠርህ አንተ ነህ፡

፲፱፡ ወእግዚእ አንተ ለኵሉ፤

የሁሉ ጌታ አንተ ነህ፤

ወአልቦ ዘይትቃወመከ እግዚእ፤

የሚቀዋወምህ ጌታ የለም፡ የሚቀዋወምህ የሌለ ፡

፳፡ ወአንተ ተአምር ኵሎ እግዚእ፤

አቤቱ ሁሉን አንተ ታውቃለህ፡

ከመ አኮ በአስተሐቅሮ፤

በመናቅ በማቃለል እንዳይ ደለ፡

አኮ በትእቢት፤

በትእቢት እንዳይደለ፡

ወአኮ በአእብዮ ርእስየ ዘገበርክዎ ለዝንቱ፤

ይህን ያደረግሁት ራሴን በማክበር እንዳይደለ አንተ ታውቃለህ፡

አላ ከመ ኢይስግድ አሐማ እቡድ፤

አዋቂ ላይደለ ሐማ እንዳል ሰግድ ነው እንጂ፡

፳፩፡ እምአብደርኩ እስዐም እገሪሁ ከመ ይሕየዉ እስራኤል፤

እስራኤል የሚድኑ ከሆኑ ጫማውን እስም ዘንድ በወደድኩ ነበር፡

አላ ገበርክዎ ለዝንቱ ከመ ኢይረሲ ክብረ ዕጓለ እመሕያው እምክብረ እግዚአብሔር፤

የሰውን ክብር ከእግዚአብሔር ክብር በላይ እንዳላደርግ ነው እንጂ፡

ወኢይስግድ ለመኑሂ ዘእንበሌከ እግዚእየ፤

ጌታዬ ካንተ በቀር ለማንም ለማን እዳልሰግድ፡

ወኢገበርክዎ ለዝንቱ በትእቢት፤

ይህነን በትእቢት ያደረግሁት አይደለም፡

፳፪፡ ወይእዜኒ እግዚኦ እግዚአ ብሔር ንጉሥ፤

አሁንም ንጉሥ የምትሆን አቤቱ ፈጣሪዬ፡

አምላከ አብርሃም መሐክ ሕዝበከ፤

የአብርሃም ፈጣሪ ወገኖችህን ይቅር በል፡



እስመ ቆሙ ላዕሌነ ያመንስዉነ፤

ያጠፉን ዘንድ በላያችን በጠላ ትነት ተነስተዋልና፡

ወፈቀዱ ያጥፍኡነ ቀዳሚተ ርስትከ፤

ኋላ በሐዲስ ተፈጥሮ በልጅነት ከምትፈጥራቸው አስቀድሞ በፍቅር ፤ በሃይማኖት የፈጠ ርኸን እኛን ያጠፉን ዘንድ ወደዋልና፡

፳፫፡ ወኢትትዐወር መክፈልተከ አንተ ቤዘውከ እምነ ምድረ ግብጽ፤

ከግብጽ ያዳንኸን ርስትህ፤ ጉልትህ የምንሆን እኛን ቸል አትበል፡

ወርስተከ፤

ማደርያዎችህን ቸል አትበል፡ ወሰአለ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ ካለው ጀምረህ ይዘህ መጥተህ ከዚህ እሥር፡ እንዲህ እንዲህ ነውና፡

፳፬፡ ስማዕ ጸሎትየ ወተሣሃል ሕዝበከ፡

ልመናዬን ሰምተህ ወገኖችህን ይቅር በል፡

ወሚጠ ለላህን ውስተ ትፍሥሕት፡

ኃዘናችንን ወደ ደስታ መል ሰው፡

ከመ በሕይወትነ ንሰብሕ ስመከ እግዚኦ፤

አቤቱ በሕይወት ሳለን ስምህን እናመሰግን ዘንድ፡

ወኢታማስን ተስፋሆሙ ለእለ ይሴፈዉከ፤

የሚታመኑብህን ሰዎች አለኝ ታቸውን አታጥፋ፡

፳፭፡ ወገዐሩ ኵሉ እስራኤል ወጸርሑ በዓቢይ ቃል በኃይሎሙ፤

ቃላቸውን አሰምተው በኃይ ላቸው ጮሁ፡

እስመ በጽሐሙ ሞት ቅድመ አዕይ ንቲሆሙ፡

ሞት በፊታቸው መጥቶባቸ ዋልና፡

፳፮፡ ወአስቴርኒ አማኅፀነት ነፍሳ ኀበ እግዚአብሔር፤

አስቴርም ሰውነቷን ከእግዚ አብሔር ዘንድ አስጠበቀች፡ አደራ ጥብቅ፤ ሰማይ ሩቅ እንዲሉ፡

እስመ ፍርኀተ ሞት በጽሐት፤

ሞትን ከመፍራት ደርሳለችና፤ የፍርሃት ድርሻ አለባትና፡

፳፯፡ ወአልባሰ ክብራ ዘትለብስ አሰሰለት ወለብሰት አልባሰ ሕማም ወላህ፡

የለበሰችውን የማዕረግ ልብሷን ትታ የኃዘን ፤ የመከራ ልብስ ለበሰች፡

www.ethiopianorthodox.org

ወህየንተ መዓዛ ትፍሥሕታ፣

በደስታዋ ጊዜ ስለምትቀባው ሽቱ ፈንታ፤

መሬተ ወሐመደ መልዐት ውስተ ርእሳ፣

በራሷ ላይ አመዱን ፣ ትቢያ ውን ሞላች፤

ወአሕመመት ሥጋሃ ጥቀ፣

ልቡናዋን እጅግ አሳዘነች፤

ወውስተ መካነ ሠርጉሃ ዘክበሰ ሥእርታ፣

ሰርመዴዋን በምታደርግበት ቦታ፤

ወወደየት መሬተ፣

ትቢያ ነሰነሰች፤

፳፰፤ ወሰአለት ኀበ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል፣

ከእስራኤል ፈጣሪ ከእግዚአ ብሔር ዘንድ ለመነች፤

ወትቤ አንተ እግዚኦ አምላክነ፣

አቤቱ ፈጣሪያችን አንተ ነህ፤

አንተ ውእቱ ባሕቲትከ ረዳኢ፤

ረዳት አንተ ብቻ የምትሆን፤

ርድአኒ ለባሕታዊት እንተ አልባቲ ረዳኢ ዘእንበሌከ፤

ካንተ በቀር ረዳት የሌላት እናት አባቴ ሙተው ብቻዬን የቀረሁ እኔን ብቻ እርዳኝ፤

እስመ በጽሐኒ ሞት ውስተ እዴከ፤

ባንተ ፈቃድ ሞት መጥቶብ ኛልና ለብቻዋ ሞት ጉልማ ድርሻ አለባትና፤

፳፱፤ ወአንሰ ሰማዕኩ እምንዕስየ በኀበ ሕዝበ አበውየ ከመ አንተ እግዚኦ ነሣእኮሙ ለእስራኤል እምነ አሕዛብ፤

አቤቱ እኔ ከሕፃንነቴ ጀምሮ እስራኤልን ከአሕዛብ ሁሉ እንደመረጥሃቸው ባባቶቼ ወገኖች ዘንድ ሰማሁ፤

ወለአበዊነሂ እምኵሉ አዝማዲሆሙ ከመ ይኩኑ ርስተ ለዓለም፤

የዘለዓለም ማደሪያ ይሆኑህ ዘንድ አባቶቻችንን ከዘመዶ ቻቸው ሁሉ እንደመረጥሃቸው ሰምቼአለሁ፤

ወይእዜኒ ገበርከ ኵሉ ዘከመ፤ ትቤ፣

ያን ጊዜ እንደተናገርህ አደረ ግህላቸው፤

፴፤ ወአበስነ በቅድሜከ፣

እኛ ግን በፊትህ በደልን፤

ወአግባዕከነ ውስተ እደ ፀርነ፣

በጠላቶቻችን እጅ ጣልኸን፤

እስመ ሰባሕነ አማልክቲሆሙ ለአሕዛብ፣

የአሕዛብን ጣዖት አመስግነ ናልና፤



ጻድቅ አንተ እግዚኦ፣

አቤቱ አንተ ቸር ነህ፤

፴፩፤ ወይእዜኒ ኢኀደጉነ፣

አሁንም አልተዉንም፤

በመሪር ቀነዩነ እለ አንሥኡ አደዊሆሙ ዲበ አማልክቲሆሙ፣

እጃቸውን ወደጣዖት ያነሡ ሰዎች በሚያሳዝን አገዛዝ ገዙን እንጂ፤

፴፪፤ ከመ ያሰስሉ ሥርዓተ አፉከ፣

ተናግረህ የሠራኸውን ሥርዓት ያጠፉ ዘንድ፤

ወያማስኑ ርስተከ፣

ማደርያዎችህን ያጠፉ ዘንድ፤ አንድም ኢየሩሳሌምን ያጠፉ ዘንድ፤

ወይፈጽሙ አፉሆሙ ለእለ ይሴብሑከ፣

አንተን የሚአመሰግኑህን ሰዎች አፋቸውን በሞት ይዘጉቸዉ ዘንድ፤

ወያጥፍኡ ስብሐተ ቤትከ በቤተ መቅደስ፣

የምትመሰገንበትን ምስጋና ያጠፉ ዘንድ፤

ወምሥዋዒከኒ፣

ምሥዋዑንም ያጠፉ ዘንድ፤

፴፫፤ ወይከሥቱ አፈ አሕዛብ ለአድልዎ ወለከንቱ፣

ከንቱ ጣዖትን ለማምለክ አሕዛብ በግብዝነት አፋቸውን ይከፍታሉ፤

ወይሴብሑ ስሞ ለንጉሥ ዘበሥጋ ዘለዓለም፤

የሥጋዊ ንጉሥን ስም ለዘለዓ ለም ያመስግኑ ዘንድ፤

፴፬፤ ወኢትመጥዎሙ ለእለ ኢሀለዉ በዘዓቀምከ፣

በሥርዓትህ ለሌሉ አሕዛብ አሳልፈህ አትስጠን፤ አንድም ለእለ ሀለውነ ይላል፤ በሥርዓ ትህ ያለን እኛን አሳልፈህ አትስጠን፤

ወኢይስሐቁ በድቀትነ፣

በጥፋታችን እንዳይዘብቱብን፤

አላ ሚጣ ለምክሮሙ ላዕለ ርእሶሙ፣

ምክራቸውን ወደራሳቸው መል ሰው እንጂ፤

ወአሕስሮ ለዘቆመ ላዕሌነ፣

በኛ ላይ በጠላትነት የተነሣ ውን አጎስቁለው፤

፴፭፤ ተዘከረነ እግዚኦ በመዋዕለ ምንዳቤነ፣

በመከራችን አስበን፤

ወኪያየኒ አጽንአኒ ንጉሠ አምላክነ፣

ፈጣሪ ንጉሥ ሆይ እኔንም አጽናኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

ዘአንተ አጽናዕከ ኵሎ ርእሰ፣

ገኘሮን ያጸናህ አንተ፤

፴፮፡ ወደይ ቃለ ሠናየ ውስተ አፉየ በቅድሜሁ ለንጉሥ፣

በንጉሡ ፊት የሚወደድ ንግግር እንድናገር አድርገኝ፤

ወሚጠ ለልቡናየ ከመ ይጽልዮ ዘጸብአነ ለገለፉ፣

ፈጽሞ የተጣላንን ይጠላው ዘንድ ልቡናውን ወደ ክፋት መልሰው፡

ወለእለ ኀብሩ ምስሌሁ፣

ከሱ ጋራ የተባበሩትን ይጠላ ዘንድ፤

፴፯፡ ወኪያነሰ አድኅነነ በእዴከ፡

እኛን ግን በሥልጣንህ አድነን፤

ወርድአኒ ሊተ ለባሕታዊት እንተ አልብየ ረዳኢ መኑሂ ዘእንበሌከ እግዚኦ፡

አቤቱ ከአንተ በቀር ማንም ማን ረዳት የሌለኝ ብቻዬን የቀረሁ እኔን እርዳኝ፤

ልበ ኵሉ ተአምር፣

የሰውን ልቡና ሁሉ መርምረህ የምታውቅ፤

፴፰፡ ወተአምር ከመ አጸልዕ ክብሮሙ ለኃጥአን፣

የአሕዛብን ክብር እንድጠላ፤

ወአስቆርር ምስካቦሙ ለቆላፉን፡

ያልተገዘሩትን ሰዎች ምንጣፍ ነታቸውን እንድጠላ፤

ወዘኵሉ ነኪር፣

ከሕግህ የተላለፈውን ሁሉ እንድጠላ ታውቃለህ፤

፴፱፡ አንተ ተአምር ምንዳቤየ፣

መከራዬን አንተ ታውቃለህ፤

ከመ ኢይዔድመኒ ሠርጐ ክብርየ ዘውስተ ርእስየ ዘቦቱ አስተርኢ በመዋዕለ ክብርየ፣

በጌትነቴ ወራት የምታይበት የማዕረግ ልብሴን ደስ ብሎኝ እንዳለብሰው፤

ወአስቈርሮ ከመ ጸርቀ ትክቶ፣

እንደ ግዳጅ ጨርቅ እንድ ጸየፈው፤

ወኢይሠረገዎ በመዋዕለ ዕረፍትየ፣

ቀኖና በያዝሁበት ወራት፡

ወክብርየ፣

በምከብርበት ቀን ደስ ብሎኝ እንዳለብሰው አንተ ታውቃለህ፤

፵፡ ወኢበልዐት አመትከ ኢማዕደ ሐማ፣

እኔ ባርያህ የሐማን ግብር አልበላሁም፤ አንድም ተረፈ መሥዋዕተ ጣዖቱን አልበላሁም፤

ወኢያስተኤድማ ስቴሁ ለንጉሥ፣

የንጉሥ መጠጥ ደስ አያሰኘኝም፤



ወኢስተይኩ እምነ ሞጻሕቶሙ፣

ከጠጃቸው አልጠጣሁም፤

፵፩፡ ወኢተፈሥሐት አመትከ በሙ እም አመ ቦእኩ እስከ ይእዜ፣

ከገባሁ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔ ባርያህ በመጠጡ ፤ አንድም በአሕዛብ ደስ አላለኝም፤

ዘእንበለ ብከ እግዚኦ አምላከ አብርሃም፣

አቤቱ የአብርሃም ፈጣሪ ከአንተ በቀር፤

፵፪፡ እግዚኦ ዘኵሎ ትክል ስማዕ ጸሎቶሙ ለቅቡፃን፣

አቤቱ ሁሉ የሚቻልህ ተስፋ ያጡ የአይሁድን ልመና ስማ፤

ወአድኅነነ እምእደ እለ አሕሰሙ ላዕሌነ፡

በኛ ክፉ ነገር ከአደረጉ ሰዎች እጅ አድነን፤

ወአድኅነኒ እምእንተ እፈርህ፣

ከምፈራው ሞት አድነኝ።

## ምዕራፍ ፮

### ጉባዔ

፩፡ ወእምዝ አመ ሣልስት ዕለት ሶበ አኅለቀት ጸልዮ፣

ከዚህም በኋላ በሦስተኛው ቀን ጸሎቷን በጨረሰች ጊዜ፤

አሰሰለት አልባሰ ላህ፣

ነገር አግኝታ የኃዘኑን ልብስ አኑራ፤

ወለብሰት አልባሰ ክብራ፣

ልብስ መንግሥቷን ለበሰች፤

ወኮነት ግርምተ፡

የምታስፈራ ሆነች፤

ወጸውአቶ ለእግዚአብሔር መድኅን ዘኵሎ ይሬኢ፣

ሁሉን የሚያድን፣ ሁሉን የሚመለከት እግዚአብሔርን ለመነችው፤

፪፡ ወነሥአት ክልኢ አዋልዲሃ፣

ሁለቱን ገረዶቿን አስከተለች፤ የምትጠላትን በኋላዋ፣ የምትወዳትን በፊትዋ አድርጋ ሄደች፤

ለአሐቲስ ትምሕካ፣

ለአንዲቱ ግን ታዝንላት ነበር፤

እስመ ታፈቅራ፣

ትወዳታለችና፤

ወካልዕታ ትተልዋ ወትፀውር አልባሲሃ፡

ሁለተኛዋ ልባልባዋን ይዛ ትከተላት ነበር፤

ወይእቲሰ ተሠነየት በኵሉ ወተረ ሰየት፣

ይህች ግን በውስጥ ፣ በውጭ አጌጠች፤ ተጠረረች፤

ወኮነ ፍሡሐ ገጻ፣

ፊቷን ደስ አለው፡

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ዘተሐውር ኀበ አዕርክቲሃ፣

ወደጠላቶቿ ስትሄድ ወደወዳጆቿ እንደሚሄድ ፊቷን ደስ አለው፡

ወልባሰ ሕዙን እምፍርኀት፣

ልቧ ግን ከፍርሃት የተነሣ አዝኖ ነበር፡

ወቦአት ኵሉ ኀተ፣

በሩን ሁሉ ገባች፡

ወበጽሐት ኀበ ንጉሥ፣

ከንጉሥ ዘንድ ደረሰች፡

ወውእቱ ይነብር ዲበ መንበረ መንግሥቱ፣

እሱ በጌትነት ዙፋኑ ተቀምጦ ነበር፡

፲፡ ወልቡስ ውእቱ አልባሰ ግርማሁ፣

ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ ነበር፡

ወኵለንታሁ በወርቅ ወበዕንቍ ዘብዙኅ ሤጡ፣

ሁለንተናው ዋጋው ብዙ በሆነ በወርቅ፣ በዕንቍ አጊጦ ነበር፡

ወግሩም ውእቱ ጥቀ፣

እጅግ ያስፈራ ነበር፡

ወተመይጠ ገጹ ምስለ ውእቱ ክብሩ፣

ልብሰ መንግሥቱን እንደለበሰ ፊቱን መለሰ፡

ወነጸራ በመዓት፣

ሳይጠራት ብትመጣ በዓይነ መዓት አያት፡

ወፈርሀት ንግሥት፡

ንግሥት ፈራች፡

ወመጽለወት ወተንተነት፣

ፊቷን ከፋው፣ ፍግምግም አለች፡

ወአስመከት ላዕለ ርእሰ ወለታ እንተ ተሐውር ቅድሜሃ፣

በፊት በፊቷ በምትሄድ በምትወዳት ገረዷ ተጠጋች፤ እሷን እግዚአብሔር ጠብቋታል፡ እንድም በምትወዳት ተጠጋች፡

፲፩፡ ወሜጠ እግዚአብሔር መንፈሰ ለንጉሥ ውስተ የውሀት፣

እግዚአብሔር የንጉሡን ልቡና ወደርኅራኄ መለሰው፡

ወተዓገሣ፣

ታገሣት፡

ወተንሥአ እመንበሩ፣

ከዙፋኑ ተነሣ፡

ወሰሐባ፣

ወደሱ አቀረባት፡

ወአንበራ ውስተ ሕፅኑ፣

ካጠገቡ አስጠጋት፡

ወአኀዘ ይየውሃ በቃል ሠናይ፣

በበጎ አነጋገር አይዞሽ እያለ ያረጋጋት ጀመረ፡



ወይቤላ ምንተ ኮንኪ አስቴር፣

አስቴር ምን ሆንሽ አላት፡

አነ እኁኪ ከመ ኢትመውቲ፣

እንዳትሞቺ እኔ ወንድምሽ ነኝ አይዞሽ አላት፡

እስመ እኩይ ሕገ ብሔርነ፡

የሀገራችን ሥርዓት ክፉ ነውና፡

ቅረቢ፡

ወደኔ ቅረቢ፡

፲፪፡ ወአንሥአ በትሮ እንተ ወርቅ ወአንበረ ውስተ ክሳዳ፣

በትረ ወርቁን አንስቶ ከአንገቷ ላይ አደረገው፣

ወሐቀፋ፣

ደገፍ አድርጎ ያዛት፡

ወይቤላ ንግርኒ፣

የሆንሽውን ንገሪኝ አላት፡

ወትቤሎ ሶበ ርኢኩከ እግዚእየ ከመ መልአከ እግዚአብሔር ደንገፀኒ ልብየ እምፍርኃተ ክብርከ፣

ጌታዬ እንደ መልአከ እግዚአብሔር ሁነህ ባየሁህ ጊዜ ጌትነትህን ከመፍራቴ የተነሣ ልቡናዬ ደነገጠብኝ፡

እስመ መድምም አንተ እግዚእ፣

አቤቱ አንተ የምታስፈራ ነህና፡

ወገጽከኒ ምሉዕ ሞገሰ፣

ፊትህም መወደድን የተመላ ነው፡

፲፫፡ ወእንዘ ትትናገር መጽለወት ወወድቀት በገጸ፣

ስትነጋገር ዝልፍልፍ ብላ ሁለተኛ በግምባሯ ወደቀች፡ እንድም የቀደመውን መልሶ መናገር ነው፡

ወደንገፀ ንጉሥ ወኵሉ ሰብኡ፡

ንጉሡና ሰዎቹ ደነገጡ ፡

ወአኀዙ ይየህዋ በቃል ሠናይ፣

በበጎ አነጋገር ያነጋግሯት ጀመር፡

፲፬፡ ወይቤላ ንጉሥ ምንተ ትፈቅዲ አስቴር፡

አስቴር ምን ላደርግልሽ ትወጃለሽ?

ወበእንተ ምንት ታስታበቍዕኒ፣

ስለምን ትለምኚኛለሽ፡

እስከ መንፈቀ መንግሥትየ ንሥኢ ለኪ ይኩንኪ፣

ላንች ይሆንሽ ዘንድ እስከ መንግሥቴ እኩሌታ ድረስ ውሰጂ አላት፡

፲፭፡ ወትቤሎ አስቴር እስመ ዕለተ በዓል ብየ፣

ዛሬ ምሳ የማደርግ ነኝና፡

ወለእመ ፈቀድከ ንጉሥ ትምጻእ ውስተ በዓልየ ዘእገብር፡

ንጉሥ ወደ አዘጋጀሁት ምሳ ልትመጣ ብትወድ፡

www.ethiopianorthodox.org

የዎም አንተ ወሐማ፣

ነዉ ያለበት ነው፤ አንተና ሐማን፤

ወእመሰ ፈቀደ፣

ከወደደስ ንጉሥ እኔ ወደ ማደርገው በዓል ይምጣ፤

ወሐማ፣

ሐማም ይምጣ፤

፶፡ ወይቤ ንጉሥ ጸውእዎ፤ ለሐማ ፍጡነ ከመ እግበር ዘትቤለኒ አስቴር፣

ንጉሡ እንዲህ አለ፤ አስቴር የነገረችኝን ነገር ፈጥኜ አደርግ ዘንድ ሐማን ፈጥናችሁ ጥሩት፤

ወሐሩ ፪ሆሙ ውስተ በዓል ዘገብረት አስቴር፣

ሁለቱም አስቴር ወደአዘጋጀ ችው ምሳ ሔዱ፤

፲፡ ወበውስተ በዓልኒ ይቤላ ንጉሥ ለአስቴር፣

በዚያ በምሳው ቀን ንጉሡ አስቴርን እንዲህ አላት፤

ምንተ ትፈቅዲ አስቴር፣

ዘአስተብቋዕክኒ እግበር ለኪ፣

አስቴር አደርግልሽ ዘንድ የለመንሽኝ ምድነው፤

፲፩፡ ወትቤሎ ስዕለትየሰ ዘአስተበቍአከ እመ ረከብኩ ሞገሰ ቅድመ አዕይንቲከ፣

የምለምንህስ ልመና በፊትህ ባለሟልነትን አግኝቼ እንደሆነ፤

ንጉሥ ወሐማ ጌሠመ ንዑ ውስተ በዓል ዘእገብር ለክሙ፣

ንጉሥና ሐማ ነገ ወደማዘጋ ጅላችሁ ምሳ ኑ፤

ወጌሠመ እገብሮ፣

ልመናዬንም ነገ እነግርህ አለሁ፤

፲፪፡ ወወፅአ ሐማ እምኀበ ንጉሥ ፍሡሐ ገጽ እንዘ ይትፌሣሕ፣

ሐማ ከንጉሡ ዘንድ ደስ ብሎት ፊቱ ብሩህ ሆኖ ወጣ፤

እንዘ ይወጽእ ሶበ ርእዮ ሐማ ለመርዶክዮስ አይሁዳዊ ተምዐ ጥቀ፣

ሲወጣ ሐማ መርዶክዮስን ባየው ጊዜ እጅግ ተቆጣ፤

፲፫፡ ወሖረ ቤቶ ወጸውዖሙ ለአዕርክቲሁ ወለሡሣሬ ብእሲቱ፣

ከቤቱ ሔዶ ወዳጆቹን፣ ሚስቱ ሡሣራን ጠራቸው፤

፲፬፡ ወአርአዮሙ ብዕሎ ወክብሮ ዘገብረ ሎቱ ንጉሥ፣

ንጉሥ ያደረገለትን ጌትነቱን ባለጸግነቱን አሳያቸው፤

ወዘከመ አዕበዮ በውስተ መንግሥቱ፣

በሚገዛው አገር እንዳከበረው እንዳገነነው፤

፲፭፡ ወይቤሎሙ ሐማ ኢጸውአት ንግሥት ምስለ ንጉሥ ወኢመነሂ ውስተ በዓል፣

ንግሥት ከንጉሡ ጋራ ማንንም ወደምሳው አልጠራችም፤



ዘእንበለ ንጉሥ፣

ከንጉሡ በቀር ፤

ወኪያየ ጸውዐተኒ፣

እኔንም ጠርታኝ ነበረች፤

፲፯፡ ወባሕቱ ሊተሰ ኢይሔውዘኒ ዝንቱ ሶበ ርኢክዎ ለመርዶክዮስ አይሁዳዊ በውስተ ዓፀድ፣

ነግር ግን ይህ ሁሉ እኔን ደስ አያሰኘኝም፤ አሁዳዊ መርዶክ ዮስን በቤተ መንግሥት ባየሁት ጊዜ ፤

፲፯፡ ወትቤሎ ሱዛራ ብእሲቱ ወአዕርክቲሁ፤ ለይግዝሙ ዕፀ ዘ፶ በዕመት፣

ሚስቱ፣ ወዳጆቹ ሃምሳ ክንድ እንጨት ይቈረጡልህ አሉት፤

ወበጽባሕ ንግሮ ለንጉሥ፣

ሲነጋ ለንጉሥ ንገረው አለችው፤

፲፰፡ ወተፈሥሐ ወዓደሞ ለሐማ ዝንቱ ነገር፣

ይህ ነገር ሐማን ደስ አሰኘው፤

ወአስተዳለወ ዕፀ፣

እንጨቱን አዘጋጀ፤ ቢቾኩል ፶ ክንድ ተራዳ ተክሏል፡፡

## ምዕራፍ ፯

፩፡ ወአንፈጸ እግዚአብሔር ንዋመ እምኔሁ ለንጉሥ በይእቲ ሌሊት፡

እግዚአብሔር ለሚያደርገው ነገር ምክንያት ይፈልጋልና በዚያች ሌሊት ከንጉሥ እንቅልፍን አራቀ ፤

ወይቤሎ ለጸሐፊሁ ያምጽእ ሎቱ መጻሕፍተ ተዝካር ዘኖብያት ዘመዋዕለ ትካት፣

ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የነበሩ የነገሥታት ወግ ታሪክ ያለበትን ታሪከ ነገሥት አምጣ አለው፤

ወያንብቡ ሎቱ ዘውስተ መጻሕፍት፣

በመጽሐፉ ያለውን ያነቡለት ዘንድ የቀደሙ ነገሥታት እንቅልፍ ያጡ እንደሆነ በሐኬት በጽርዓት አያድሩም ነበር፤ ታሪከ ነገሥት ያስነብቡ ነበርና ታሪከ ነገሥት አምጣ አለው፤

፪፡ ወእምዝ ረከቡ በውስተ መጽ ሐፉ ኀበ ጸሐፉ በእንተ መርዶክዮስ ዘከመ ዜነዎ ለንጉሥ በእንተ ፪ቱ ሕጽዋኒሁ ለንጉሥ እለ የዐቅብዎ ለንጉሥ፣

ከዚህ በኋላ የመርዶክዮስን ነገር በጻፉበት መጽሐፍ ንጉሡን የሚጠብቁ የንጉሥ የሁለቱ ባለሟሎቹን ነገር ለንጉሥ እንደነገረው አገኙ፤

ወፈቀዱ ይቅትልዎ ለአርጤክስስ፤

አርጤክስስን ሊገድሉት እንደ ወደዱ አገኙ፤ ይህ ሲነበብ ሲተረጐም ከዚህ ደርሷል፤ አንድም መጀመሪያ በተአም ራት ይህ ወጥቷል፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፡ ወይቤ ንጉሥ አይ ክብር ወጸጋ ዘገበርነ ሎቱ ለመርዶክዮስ፤

ንጉሥ ለመርዶክዮስ ያደረግ ንለት ስጦታ ክብር ምንድነው? አለ፤

ወይቤልዎ ደቂ ለንጉሥ አልቦ ዘገበርከ ሎቱ እግዚኦ፤

ብላቴኖች አቤቱ ለመርዶክዮስ ያደረግህለት የለም አሉት፤

፬፡ ወእንዘ ይትናገር ንጉሥ አኰቴቶ ለመርዶክዮስ በጽሐ ሐማ ኀበ ንጉሥ፤

ንጉሥ የመርዶክዮስን ምስጋና ሲናገር ሐማ ከቤተ መንግሥት አደባባይ ደረሰ፤

ወይቤ ንጉሥ መኑ ዝ ዘውስተ ዓፀድ፤

ንጉሡ ነገዱ ሰምቶ ካዳራሽ የቆመ ማነው አለ፤

ወይቤልዎ ሐማ፤

ሐማ ነው አሉት፤

፭፡ ወእምዝ ቦአ ሐማ፤

የተላለፈ ነው፤

ይንግሮ ለንጉሥ ከመ ይስቅሎ ለመርዶክዮስ ውስተ ዕፅ ዘአስተዳለወ፤

ከዚህ በኋላ ባዘጋጀው ተራዳ ላይ መርዶክዮስን ይሰቅለው ዘንድ ሐማ ለንጉሡ ይነግረው ዘንድ ገባ፤

፮፡ ወይቤልዎ ደቂቀ ለንጉሥ ናሁ ሐማ ይቀውም ውስተ ዐፀድ፤

የንጉሥ ብላቴኖች እነሆ ሐማ ከደጅ ቁሟል ብለው ነገሩት፤

ወይቤ ንጉሥ ጸውእዎ፤

ንጉሡ ጥሩት አለ፤ ወእምዝ ቦአ ሐማ ብለህ ግጠም፤

፯፡ ወይቤሎ ንጉሥ ለሐማ ምንተ እግበር ሎቱ ለብእሲ ዘአነ አፈቅር አክብሮ፤

ንጉሡ ሐማን አከብረው ዘንድ እኔ ለምወደው ሰው ምን ይገባዋል አለው፤

ወይቤ በልቡ ሐማ መነ ያፈቅር ያክብሮ ንጉሥ ዘእንበለ ኪያየ፤

ሐማ በልቡ ከኔ በቀር ንጉሥ የሚወደው ማን አለ ብሎ፤

ወይቤሎ ለንጉሥ ለብእሲ ዘይፈቅድ ንጉሥ ያክብሮ፤

ንጉሥ ያከብረው ዘንድ የወደ ደውን ሰው፤

ያምጽኡ ሎቱ ደቀ ንጉሥ ሚላተ ዘይለብሶ ንጉሥ፤

የንጉሥ ብላቴኖች ንጉሥ የሚለ ብሰውን ነጭ ሐር ያምጡለት፤

ወፈረሰ ዘይጼዕን ንጉሥ፤

ንጉሡ የሚቀመጥበትን ፈረስ ያምጡለት፤

፰፡ ወየሀብዎ ለአሐዱ እምአዕ ርክቲሁ ለንጉሥ እለ ክቡራን፤

ከከበሩ ከንጉሥ ባለሚሎች ለአንዱ ይስጡት፤



ወያልብስዎ ለውእቱ ብእሲ ዘያፈቅር ንጉሥ፤

ንጉሥ የሚወደውን ሰው ያልብሰው፤

ወያዕዕንዎ ዲበ ፈረሱ፤

በፈረሱ ላይ ያስቀምጡት፤

ወይስብክ ሎቱ ዓዋዲ ውስተ መርህበ ሀገር፤

አዋጅ ነጋሪ በአደባባይ አዋጅ ይንገርለት፤

እንዘ ይብል ከመዝ ይከውን ሎቱ ለብእሲ ዘንጉሥ አክበሮ፤

ንጉሥ ያከበረው ሰው እንዲህ ይሆንለታል ብሎ፤

፱፡ ወይቤሎ ንጉሥ ለሐማ ሠናየ ትቤ ግበር ሎቱ ከማሁ ለመርዶ ክዮስ አይሁዳዊ ዘይፀመድ ውስተ ዓፀድ፤

ንጉሥ ሐማን በጎ ነገር ተናገርህ አሁን እንደተናገርህ በቤተ መንግሥት ለሚያገለግል ለመርዶክዮስ አድርግለት፤

ወኢትሕድግ አሐተ ቃለ እምዘ ነበብከ፤

ከተናገርከው አንዲት ቃል አታስቀር አለው፤

፲፡ ወነሥአ ሐማ አልባሰ ወፈረሰ፤

ሐማ ፈረሱን ልብሱን ተቀብሎ፤

ወአልበሶ ለመርዶክዮስ፤

መርዶክዮስን አለበሰው፤

ወአጽአኖ ዲበ ፈረስ፤

በፈረስ ላይ አስቀመጠው፤

ወአየደ ውስተ መርህበ ሀገር፤

በአደባባይ አዞሮ፤

ወሰበከ እንዘ ይብል ከመዝ ይሬሲ ንጉሥ ለኵሉ ብእሲ ዘፈቀደ ያክብሮ፤

ንጉሥ ያከብረው ዘንድ ለወደደው ሰው ሁሉ እንዲህ ያደርግለታል ብሎ አዋጅ ነገረ፤

፲፩፡ ወእምዝ ገብአ መርዶክዮስ ውስተ ዐፀድ፤

ከዚህ በኋላ መርዶክዮስ ወደቤተ መንግሥት ተመለሰ፤

ወሐማኒ አተወ ቤቶ እንዘ ያቴሕት ርእሶ፤

ሐማም አንገቱን ደፍቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤

፲፪፡ ወነገራ ሐማ ለሰዛራ ብእሲቱ ወለአዕርክቲሁ፤

ሐማ ለሚስቱ ለሰዛራ ነገራት፤ ለወዳጆቹም ነገራቸው፤ ሁሉ ሲሰግድልኝ መርዶክዮስ የሚባል አይሁዳዊ ሳይሰግ ድልኝ ቀረ ብሎ፤

ወይቤልዎ አዕርክቲሁ ወብእሲቱ፤

ሚስቱ ወዳጆቹ እንዲህ አሉት፤

www.ethiopianorthodox.org

እመሰ ለመርዶክዮስ ዘእምዘመደ አይሁድ ተትሕትከ ሎቱ ቅድሜሁ ወደቀ፤

ለአይሁድ ወገን ለሚሆን ለመ ርዶክዮስ ራስህን ካዋረድህ እንዳዋረድህ መቅረትህ ነው፤

ወኢትክል መዊዖቶ፤

እሱን ማሸነፍ አይቻልህም፤

እስመ እግዚአብሔር ምስሌሁ፤

እግዚአብሔር በረድኤት ከሱ ጋራ አለና፤

፲፬፤ ወአጕጕዕዎ ለሐማ ውስተ በዓል ዘገብረት አስቴር፤

ሐማን አስቴር ወደአዘጋጀችው ምሳ ለመምጣት አስቸኰሉት።

## ምዕራፍ ፯

፩፤ ወቦአ ንጉሥ ወሐማ ይምስሐ ምስለ ንግሥት፤

ከንግሥት ጋራ ምሳ ይበሉ ዘንድ ንጉሥና ሐማ ገቡ፤

፪፤ ወይቤላ ንጉሥ ለአስቴር አመ ሳኒታ በዓል፤

ንጉሥ አስቴርን በሁለተኛው ቀን በዓል እንዲህ አላት፤

ምንት ኮንኪ አስቴር፤

አስቴር ምንሆንሽ፤

ወምንት ውእቱ ስዕለትኪ፤

ልመናሽ ምንድር ነው፤

ወምንት ውእቱ ዘአስተብቍዕክኒ፤

የለመንሽኝ ልመና ምንድር ነው፤

ወሶበ ፈቀድኪ መንፈቀ መንግሥትየ እምወሀብኩኪ፤

ከወደድሽ የመንግሥቴን እኩሌታ በሰጠሁሽ ነበር አላት፤

፫፤ ወአውሥአቶ ወትቤሎ፤

መለሰችለት፤ እንዲህ አለችው፤

እመሰ ረከብኩ ሞገሰ በቅድመ ንጉሥ፤

በንጉሥ ፊት ባለሟልነት አግኝቼ እንደሆነ፤

ይትወሀባ ለነፍስየ ስእለታ ወቃለ አስተብቊዖትየ፤

የልመናዬን ነገር፤ የልቡናዬን አሳብ አድርግልኝ፤

፬፤ እስመ ተሰየጥነ አነ ወሕዝብየ፤

ወገኖቼና እኔ ተሸጠናልና፤

ወኮነ ለሞት፤

ሞት ተፈርዶብናልና፤

ወለተበርብሮ፤

ለመበዝበዝ ሁነናልና፤

ወለቅንየት ንሕነ ወውሉድነ፤

እኛም ልጆቻችንም ለመገዛት ሁነናልና፤



ወአርመምኩ እስመ ኢይደልዎ ለመስተዋድይ ይባእ ውስተ አፀደ ንጉሥ፤

ነገረ ሠሪ ወደንጉሥ ከተማ መግባት አይገባውምና ነገር ሠሪ እመስል ብዬ ዝም አልኩ፤ አንድም ነገረ ሠሪ ሐማ ወደንጉሥ መግባት አይገባውምና ምንም ባይገባው ጊዜ ይግለጠው ብዬ ዝም አልኩ፤

፭፤ ወይቤ ንጉሥ መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘተሀበለ ይግበር ዘንተ ግብረ፤

ንጉሥ እንዲህ አለ፤ ይህን ሥራ ይሠራ ዘንድ የደፈረ ማነው፤

፮፤ ወትቤ አስቴር ዝኩ ብእሲ ጸላዒነ ሐማ፤

አስቴርም ጥንተ ጠላታችን ሐማ ነው አለችው፤

ወሶበ ሰምዐ ሐማ ፈርሀ እምነ ንጉሥ ወእምነ ንግሥት፤

ሐማ ይህን በሰማ ጊዜ ከንግሥትና ከንጉሡ የተነሳ ፈራ፤

፯፤ ወተንሥአ ንጉሥ እምነበ ይሰቲ፤

ለሷ ምላሽ ሳይመልስላት ንጉሥ ከሚጠጣበት ተነስቶ፤

ወቦአ ውስተ ገነት፤

ተክል ለማየት ገባ፤

ሐማሰ አስተብቍዓ ለንግሥት፤

ሐማ ግን ንግሥትን ማለዳት፤

እስመ አእመረ ከመ በጽሐቶ እኪት፤

መከራ እንደደረሰችበት አውቋልና በዚህ ጊዜ ሐማ ከጥግ ሁኖ ይሰማ ነበረ፤ ገብቶ አንቺ የሰቀልሽውን አንቺ አውርጂው ብሎ ከእግሯ ወደቀ፤

፰፤ ወገብአ ንጉሥ እምነ ገነቱ፤

ንጉሥ ከተክሉ ቦታ ተመለሰ፤

ሐማሰ ወድቀ ውስተ አራት ወይትጋነይ ላቲ ለንግሥት፤

ሐማ ግን ከዙፋኑ ሥር ወድቆ ንግሥትን ይለምን ነበር፤

ወይቤሎ ንጉሥ ብእሲትየኒ ትትገዒለኒ በቤትየ፤

ያደረግኸኝ ነገር አልበቃህ አለና ሚስቴን ከቤቴ ልትቀማኝ ነው? አለው፤

ወሶበ ሰምዐ ሐማ ዐልመ ገጹ፤

ይህን በሰማ ጊዜ ሐማ ፊቱ ጠቆረ፤

፱፤ ወይቤ ቡክታን አሐዱ እምሕፅዋኒሁ ለንጉሥ ሀለወ ዕፅ ዘአስተዳለወ ለመርዶክዮስ ዘአይድአነ በእንተ ንጉሥ፤

ከንጉሡ ባለሟሎች አንዱ ቡክታን እንዲህ አለ፤ የንጉሥ ያንተን ነገር የነገረን ለመርዶ ክዮስ ያዘጋጀው መስቀል አለ አለ፤

www.ethiopianorthodox.org

ዕፅሰ ትኩል ውስተ ቤተ ሐማ ዘ፶ በእመት፤

ቁመቱ አምሳ ክንድ የሚሆን መስቀል ግን ከሐማ ደጃፍ ተተክሏል አለው፡

ወይቤ ንጉሥ ይስቅልዎ ቦቱ፤

ንጉሥ በመስቀል ይስቀሉት አለ፤

፲፡ ወሰቀልዎ ዲበ ውእቱ ዕፅ ዘአስተዳለወ ለመርዶክዮስ፤

ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ዕፅ /ተራዳ ላይ/ ሰቀሉት፡

ወእምዝ ኀደገ ንጉሥ መዓቶ ለመርዶክዮስ፡

መርዶክዮስን የተቆጣውን ቁጣ ተወ ማለት እስራኤልን አጥፋ ማለቱን ተወ።

## ምዕራፍ ፰

፩፡ ወበይእቲ ዕለት ጸገዋ ንጉሥ አርጤክስስ ለአስቴር ኵሎ ንዋየ ለሐማ መስተዋድይ፡

በዚያች ቀን ንጉሡ አርጤክስስ የነገረ ሠሪ የሐማን ገንዘብ ሁሉ ለአስቴር ሰጣት፤

ወጸውዖ ንጉሥ ለመርዶክዮስ፤

ንጉሥ መርዶክዮስን ጠራው፤

ወአይድዓቶ አስቴር ለንጉሥ ከመ በቤቱ ልህቀት፤

አስቴርም በመርዶክዮስ ቤት እንዳደገች ለንጉሡ ነገረችው፤

፪፡ ወነሥአ ንጉሥ ኅልቀቶ ዘነሥአ እምእደ ሐማ፤

ንጉሡ ከሐማ እጅ የተቀበ ለውን ሐቲም ቀለበት፡

ወወሀቦ ለመርዶክዮስ፤

ለመርዶክዮስ ሰጠው፤

ወሚመቶ አስቴር ለመርዶክዮስ ላዕለ ኵሉ ዘሐማ፤

አስቴር መርዶክዮስን በሐማ ገንዘብ ላይ ሾመችው፤

፫፡ ወእምዝ ጸገመ ነበበቶ ለንጉሥ ወአስተብቍዐቶ፤

ዳግመኛ ንጉሡን ተናገረችው፤ ለመነችው፤

ወሰገደት ታሕተ እገሪሁ ከመ ይህድግ ኵሎ እኪተ እንተ ገብረ ሐማ ላዕለ አይሁድ፤

ሐማ በአይሁድ ላይ ያደረገውን ነገር ይቅር ይል ዘንድ ከእግሩ በታች ሰገደች፤ የቀደመውን መናገር ነው፤ አንድም ሁለተኛ ነው፤

፬፡ ወአንሥአ ንጉሥ በትሮ ዘወርቅ ወአንበረ ዲበ ርእሳ ለአስቴር፤

የወርቁን ዘንግ አንሥቶ በአስቴር ላይ አስቀመጠው ማለት በወርቁ ዘንግ ነካ ነካ አደረጋት፤

ወተንሥአት ወቆመት ቅድመ ንጉሥ፤

ተነሥታ በንጉሥ ፊት ቆመች፤



፭፡ ወትቤሎ አስቴር ለእመ ትፈቅደኒ፤

አስቴር እንዲህ አለችው፡ እኔን ትወደኝ እንደሆን፤

ወረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ፤

በፊትህ ባለሟልነትን አግኝቼ እንደሆነ፤

ለአከ ያምጽኡ መጻሕፍተ ዘጸሐፈ ሐማ ከመ ይቅትልዎሙ ለአይሁድ በውስተ መንግሥትከ፤

በምትገዛው ሀገር ያሉ አይሁድን ያጠፉ ዘንድ ሐማ የጻፈውን ደብዳቤ መልሰው ያመጡ ዘንድ ላክ አለችው፤

፮፡ ወእፎ እክል እርአይ እኪቶሙ ለሕዝብየ፤

የወገኖቼን ጥፋት አይ ዘንድ እንደምን ይቻለኛል፤

ወእፎ እክል ሐይወ እምድኅረ ሞቶሙ ለሕዝብየ፤

ወገኖቼ ከሞቱ በኋላ በሕይወት መኖር እንደምን ይቻለኛል አለችው፤

፯፡ ወይቤላ ንጉሥ ለአስቴር ናሁ ኵሎ ንዋዮ ለሐማ ወሀብኩኪ ወጸገውኩኪ፤

ንጉሡም አስቴርን እነሆ የሐማን ገንዘብ ሁሉ ሰጠሁሽ አላት፤

ወኪያሁ ሰቀልክዎ ዲበ ዕፅ፤

እሱንም በመስቀል ሰቀልሁት፤

እስመ አንሥአ እዴሁ ላዕለ አይሁድ፤

እስራኤልን አጥፏቸው ብሎ ቃሉን ከፍ ከፍ አድርጓልና፤

ምንተ ትፈቅዲ እንከ፤

እንግዲህ ምን ላደርግልሽ ትወጃለሽ፤

ይጽሐፉ እንከሰ በስምየ ወይኅትሙ በማኅተምየ ዘከመ ትፈቅዲ፤

ከእንግዲህ ወዲህስ አንቺ እደምትወጂው አርጤቅስስ እንዲህ አለ፤ ብለው በስም ይጻፉ ያትሙ፤

፰፡ እስመ ኵሉ ዘተጽሕፈ በትእዛዘ ንጉሥ ወተሐትመ በማኅተምየ አልቦ ዘየአቢ፤

በንጉሥ ትእዛዝ ተጽፎ በኔ ማኅተም የታተመውን እንቢ የሚል የለምና፤

፱፡ ወጸውዐ ጸሐፍተ በቀዳሚ ወርኅ ኒሳን እመ፲ወ፫ቱ ዓመት፤

ከነገሠ ባሥራ ሦስተኛው ዘመን በመጀመሪያ ወር በሚያዝያ ጸሐፍቱን ጠራ፤

ወጸሐፉ ለአይሁድ ዘከመ አዘዞሙ ንጉሥ ለመገብቱ ወለመኳንንቱ፤

ንጉሥ ለሹማምንቱ ለመኳን ንቱ ለመሳፍንቱ እንዳዘዛቸው ለአይሁድ ጻፉ፤

እምነ ህንደኬ እስከ ኢትዮጵያ፤

ከህንደኬ ጀምሮ እስከ ኢትዮ ጵያ ድረስ ላሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

በበበሐውርቲሁ በበነገረ ብሔሮሙ፣

በየቋንቋቸው ለየሀገሩ ጻፉ፤

፲: ወጸሐፉ በቃለ ንጉሥ፣

አርጤክስስ እንዲህ አለ ብለው ጻፉ፤

ውንተሙ በማኅተሙ፣

በማኅተሙ አተሙት፤

፲፩: ወፈነወ መጻሕፍቲሁ ምስለ ሐዋርያት ከመ አዘዞሙ ይግበሩ፣

በስሙ ይጽፉ ዘንድ እንዲ ዘዛቸው መጻሕፍቱን ከመላክ ተኞች ጋራ ሰደዱ፤

ለኵሉ በሐውርት ወአህጉር፣

በከተማም በገጠርም ላሉ ላኩ፤

ይርድእዎሙ ወይዕቀብዎሙ እምእደ ፀሮሙ፣

እስራኤልን ይረዷቸው ዘንድ ከጠላቶቻቸው እጅ ይጠብቁ ዋቸው ዘንድ፤

ወእምእለ ይቀውሙ ላዕሌሆሙ፣

በነዚያ ላይ በጠላትነት ከሚነሱ፤

በከመ ፈቀዱ እሙንቱ በይእቲ ዕለት፣

በዚያች ቀን እነሱ ይገድሏቸው ዘንድ እንደወደዱ ፤

፲፪፡ በኵሉ መንግሥተ አርጤክስስ፣

አርጤክስስ በሚገዛው ሀገር ሁሉ ላሉ፤

አመ ፲ወ፫ ለሠርቀ አዳር ዘ፲ቱ ወ፬ቱ፣ አውራኁ፣

በዐሥራ ሁለተኛ ወር መጋቢት በባተ ባሥራ ሦስት ቀን፤

፲፫: ኀበ ተጽሕፈ እማንቱ መጻሕፍት ንጉሥ ዓቢይ አርጤክስስ፡

እኒህ የተጻፉ ገናና የሚሆን የአርጤክስስ መጻሕፍት፤

ለብሔረ ህንደኬ ወለኢትዮትጵያ

በህንደኬ፣ በኢትዮጵያ አውራጃ ላሉ ይድረሳቸው፤

ለ፻ ፳ወ፯ቱ በሐውርት፤

ለመቶ ሐያ ሰባት አህጉር፤

ወለመሳፍንት ወለመኳንንት፤

ለመሳፍንቱ፣ ለመኳንንቱ ይድ ረሳቸው፡፡

## ምዕራፍ ፲

### ገባዔ

፩፡ በመልእክተ ዚአነ ይግበሩ ትፍሥሕተ ለከሙ ብዙኃ በአፈድፍዶ ለእለ ይበቍለዎሙ በአስተምሕሮ፤

ትበቍዕዎሙ ሲል ነው፣ በኛ ደብዳቤ አሕዛብን በማስተማር የምትረቧቸው የምትጠቅሟ ቸው ለናንተ ብዙ ተድላ ደስታ ያድርጉላችሁ፤ አንድም ለምትረቧቸው ለናንተ በማዘን የነበሩ ብዙ ሰዎች በኛ ክታብ መምጣት ለናንት ተድላ ደስታ ያድርጉ፤



ወበ አፍጥኖ ሚመት አብዝኁ ትዕቢተ፤

እለ ሐማ ፈጥነው ሹመትን በማግኘት ትዕቢትን አበዙ፤

፪፡ ወአኮ ለእለ ይትኴነኑ ለነ በእንቲአሆሙ ዘይፈቅዱ ያሕሥሙ ላዕሌሆሙ፣

የበደሉ የሚገዙልንን አይሁድን ብቻ የበደሉ አይደለም፤

ወጽጋቦሙ ኢይክሉ ፀዊረ፣

ጥጋባቸውን መታገስ የማይችሉ እለሐማ ጽጋቦሙ ባለው ራፍቆሙ ይላል፤

አላ ለእለ ይበቍዕዎሙ ይሔልዩ ዘከመ ይትሚነይዎሙ፣

አላ አሁን ቀሪ ነው፤ የምንረባ ቸው የምንጠቅማቸው እኛንም ነው እንጂ፤ አንድም አላን ለማ ውጣት ጥጋባቸውን የማይችሉ ክፉ ሊያደርጉ የሚወዱ እለ ሐማ ለኛ በሚገዙ ለአይሁድ ብቻ አይደለም አላ፤ ለእለ ይበቍዕዎሙ በመገዛት በሚጠ ቅሟቸውም ሊተነኮሉ ያስባሉ እንጂ፤

፫፡ ወአኮ አኰቴተ ሰብእ ዘይክሕዱ ባሕቲቶ፣

የመርዶክዮስን ምስጋና ብቻ የሚክዱ አይደለም፤

ወዓዲ ከመ ሐዲሳነ ብዕል ያሌዕሉ ርእሶሙ በትዕቢት፡

ዳግመኛም ሐዲሳነ ብዕል እንደ መሆናቸው በትዕቢት ራሳቸ ውን ያከብራሉ፣ ያገናሉ እንጂ፤

ወለእግዚአብሔርኒ ዘኵሎ ይእኅዝ ዘልፈ ይክሕዱ፣

ሁሉን እንደጥና፣ እንደ እንቁ ላል የሚይይዝ እግዚአብሔ ርንም ሁልጊዜ ይክዱታል፤ እንጂ፤

ወእምእግዚአብሔር ጻላዔ እኪት ይመስሎሙ ዘየመስጡ እምኵ ነኔሁ፣

ክፉትን፣ ኃጢአትን ከሚጠላ ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚያ መልጡ ይመስላቸዋልና፤

፬፡ ወመብዝሕቶሙ ባሕቲ ለብዙኃን ለእለ ይትኴነኑ ወሥሩዓን ለእለ ተአመናሆሙ ይትኴነኑ በተአኅዎ ከመ ይትለአኩነ እሙንቱ ተሳተፉ ላዕለ ደም ንጹሕ፣

ከአሕዛብ የሚበዙ አሕዛብ፣ አንድም ከእሥራኤል የሚበዙ እስራኤል ይገዙልን ዘንድ የም ናምናቸው አይሁድን ደማቸ ውን በማፍሰስ ከሐማ ጋራ አንድ ሆኑ፤

ወሠርዑ ላዕሌሆሙ ሕማመ ዕፁበ፣

በሳቸው ላይ ጭንቅ መከራ አመጡባቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ በሐልዮ እኩይ ወበሐስዎ ምክር፡

ክፉ ነገር በማሰብ በሐሰተኛ ምክር ፡

ኀዪጠሙ መንግሥተ እንተ ትትነበር በየውሃት ወበኀድአት፤

በየውሃት በጸጥታ የምትኖር መንግሥትን በማታለል፡

፮፡ ወባሕቱ በሐልዮ ይከውን ሰላም፤

ነገር ግን አሳብ ሁኖ ይቀራል፤

ወአኮ ከመናፈድፍድ እምነ ዘትድሚነ ዘከመ ተወፈይነ ሐሳቦሙ ከማሁ ሀለውነ፡

ከኛ አስቀድሞ ከነበሩ ከአባቶቻችን ሥርአት እኛ የምን በልጥ አይደለም፤ የአባቶቻችንን ሥርዓት ሥርዓት አድር ገን በዚያው ጸንተን እንኖ ራለን እንጂ፡

፯፡ ወእምድኅረ ዝንቱ ባሕቱ ነሐሥሥ ዘተገብረ ዘእንበለ ሕግ፤

ነገር ግን ከዚህ በኋላ ያለ ሥርዓት የተደረገውን እንመረ ምራለን፤

እስመ ረከቡ ክብረ ዘኢይደልዎሙ እለ ኢይክሉ ርቱዐ ኰንኖ፤

የቀና ፍርድ መፍረድ የማይቻ ላቸው ሰዎች መንግሥትን አግኝተዋልና፡

፰፡ ወሐለይነ እምድኅረ ዝንቱ በዘትትነበር መንግሥትነ ዘእንበለ ሀውክ፤

ከዚህም በኋላ መንግሥታችን ያለሁከት ጸንታ በምትኖር ገንዘብ በግፍ የተደረገውን ነገር መረመርን፡

ወበዚይትራታእ ንብረተ አሕዛብ፡ ወዘሰ ያስተርኢ ዘልፈ ንኴንን በየውሃት፤

የኛ የአሕዛብ አነዋወራችን ፀንቶ በሚኖር ገንዘብ የተገለጠ ውንም ፍርድ ዘወትር በየውሃት ጸንተን እንፈርዳለን፡

፱፡ ወከመ ሐማስ ወልደ አምዳቱ መቄዶናዊ፤

ጥንቆላ የተማረ የአምዳቱ ልጅ ሐማ ግን፡

ውጹእ ውእቱ እምጽድቅ፤

ከእውነት ፍርድ የወጣ እንደ መሆኑ፡

ወእምቅድመ ፋርስ ርኁቀ ኮነ፤

ከፋርስ ሥራት የራቀ እንደ መሆኑ፡

ብዙኀ እምኒፉትነ፤

እኛ ለሱ፤ እሱ ለኛ ከሚያደ ርገው በጐነት የራቀ እንደ መሆኑ ፡

ወኮነ ነኪረ እንዘ ንበር ውስቴትነ፤

ከኛ ጋራ ሳለ ባዕድ ሆነ፡



፲፡ ረኪቦ ውእቱኒ እንተ ላዕለ ኵሉ ሕዝብ ሚመተ ወምሕረተ፤

ከሰው በላይ የምታደርግ ሹመትን ባለሚልነትን አግኝቶ፡

ወዘፈድፋደሰ ሚመተረከበ እስከ አቡነ ንብሎ፤

አባታችን እስክንለው ድረስ ይልቁንም ሹመትን አግኝቶ፡

ወዳግመ መንግሥትነ፡

የመንግሥታችን ሁለተኛ የሚሆን፡ አንድም መድምመ በመንግሥታችን የተደነቀ አባታችን እስክንለው ድረስ፡

ወምስለ መንበር ረኪቦ፡

ከሹመት ጋራ ባለሚልነትን አግኝቶ፡

፲፩፡ ዓዲ ኢአከሎ ዝንቱ፡

ከሰጠነው ሹመት ጋራ አባታ ችን ማለት ይህ አልበቃው ብሎ፡

አላ አእበየ ተዐብዮ፡

አብዝኃ ሲል ነው፡ ትዕቢትን አበዛ እንጂ፡

ወሐለየ ያውጽአነ እመንግሥትነ፡

ከመንግሥታችን ይለየን ዘንድ አሰበ፡

ወይትማልአነ ነፍስነ፡

ሰውነታችንን ያጠፋ ዘንድ አሰበ፡

፲፪፡ ወለመርዶክዮስ ዘበኵሉ ይበቀአነ ወይፌውሰነ፤

ጸበል እየረጨ የሚረባን የሚጠቅመን መርዶክዮስን፡

ወያሰ ልጥለነ፡

ችግራችንን የሚፈጽምልንን፡

ወለአስቴርኒ ሱታፌ መንግሥትነ ዘእንበለ ኀኒስ፡

ነውር፤ ነቀፋ የሌላትን የመን ግሥታችን ተባባሪ የምትሆን አስቴርን፡

ምስለ ኵሉ ሕዝቦሙ፡

ነውር ነቀፋ ከሌላቸው ከእሥራ ኤል ጋራ፡

በብዙኅ ተመይኖ፡

በብዙ መተንኮል፡

ወበአስተጥእሞ ነገር፡

ነገር በማጣፈጥ ፡

ስእነ ያማስኖሙ፤

ማጥፋት ተሳነው፡

፲፫፡ ወበይነ ዝንቱ ነገር እስመ በየውሃት ንነብር ረኪበነ መንግሥተ ፋርስ፡

የፋርስን መንግሥት አግኝተን ስለዚህ ነገር በየውሃት እንኖ ራለን፡

ወውእቱሰ ፈቀደ ያፍልሰነ በሕገ መቄዶናዊ፤

እሱ ግን የመቄዶንያ ሰዎች በሚጠነቁሉት ጥንቁላ እስራ ኤልን ያጠፋቸው ዘንድ ወደደ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፡ ወንሕነሰ ባሕቲቱ ለእለ ፈቀደ ያማስኖሙ ለአይሁድ፤

ነገር ግን ያጠፋቸው ዘንድ የወደደ አይሁድን፤

ረከብናሆሙ ከመ አኮ በእከዮሙ፤

ያጠፋቸው ዘንድ የወደደ በክፋታቸው እንዳይደለ አገኘናቸው፤

አላ በጽድቅ ንብረተ ሕጎሙ፤

በእውነተኛ ሕግ ጸንተው ስለ ኖሩ ነው እንጂ፤

፲፭፡ ወአማን ውሉደ እግዚአብሔር ልዑል ወዓቢይ ወሕያው፤

ሕያው፣ ገናና፣ ልዑል የሚሆን በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆኑ ነው እንጂ፤

ዘያስተዴሉ ለነ፤

መንግሥትን ያዘጋጀልን፤

ወለእለ ዘቅድሜነ መንግሥተ፤

ከኛም አስቀድመው ለነበሩ መንግሥትን ያዘጋጀ፤

ወለነኒ፤

ዘከመ ልብነ ለማለት ደግሞ ታል፤ ለኛም መንግሥትን ያዘጋጀልን፤

፲፮፡ ወሠናይ ባሕቲቱ ለእመ ኢሰማዕክሙ ትእዛዘ ሐማ ወልደ አምዶቱ፤

የአምዶቱ ልጅ የሐማን ነገር ባትሰሙ የኔን ነገር ብትሰሙ መልካም ነው፤

ወቃለ መጽሐፉ ዘፈነወ፤

የላከውን የመጽሐፉን ነገር ባትሰሙ በጎ ነው፤

፲፯፡ እስመ ለሊሁ ውእቱ ሐለዮ ለውእቱ ግብር፤

ይህንን ሥራ እሱ አስቦታልና፤

በቅድመ አንቀጸ ሱሳ ሀገር፤

ሱሳ በሚባል ሀገር አደባባይ፤

ተጸልበ ምስለ ኵሉ ሰብኡ፤

ከቤተሰቦቹ ጋራ ተሰቀለ፤ ተፀልበ ባለው ተጸብለ ይላል፤ ተሰቅለ ማለት ነው፤

እስመ ፍዳሁ ዘኵሉ ይመልክ እግዚአብሔር ፍጡነ ፈደዮ ኵነኔሁ፤

ፍዳሁና ኵነኔሁ አንድ ወገን፤ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ፍዳውን አምጥቶበታልና፤ አንድም ፍዳሁ፤ በኵነኔሁ በሚፈርድበት ጊዜ ፍዳውን አምጥቶበታልና፤

፲፰፡ ወአርእይዋ ለዛቲ መጽሐፍ ሰፊሐክሙ በኵሉ መካነ ገሐደ፤

ይህችን መጽሐፍ በየቦታው ሁሉ ባደባባይ ዘርግተው አሳዩዋት፤

ወኅድግዎሙ ለአይሁድ ይንበሩ በከመ ሕጎሙ፤

አይሁድን እንደሕጋቸው ይኖሩ ዘንድ ተዋቸው፤



ወርድእዎሙ በመዋዕለ ምንዳቤሆሙ ዘአጠቅዎሙ ቀዲሙ፤

በመከራቸው ወራት ባስጨነቋቸው ጊዜ አስቀድማችሁ እርዷቸው፤ አንድም ርድእዎሙ ቀዲሙ ባሳጨነቋቸው በመከራቸው ወራት ፈጥናችሁ እርዷቸው፤

አመ፲ ወ፫ ለሠርቀ አዳር ዘ፲ቱ ወ፪ቱ አውራኅ፤

ባሥራ ሁለተኛ ወር በመጋቢት፣ መጋቢት በባተ ባሥራ ሦስት ቀን፤

፲፱፡ ወእምይእቲ ዕለት እስከ ዛቲ ሰዓት ዘእምኵሉ ይጸንዕ እግዚአብሔር ህየንተ ሙስናሆሙ ለሕዝብ ኅሩያን ዘገብረ ሎሙ ትፍሥሕተ፤

ከዚያች ቀን ጀምሮ እስከዚህ ሰዓት ድረስ ከሁሉ የሚጸና እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ጥፋት ፈንታ ተድላ ደስታ አደረገላቸው፤ አንድም ዘኵሉ ያጸንዕ ይላል፤

፳፡ ወአንትሙኒ ከመ ስሙይ በአላቲክሙ፤

የታወቁ በዓለ ሠዊትን፣ በዓለ መጸለትን እንድታከብሩ፤

ወፍሉጥ ዕለት፤

በዓለ ፋሲካን እንድታከብሩ፤

ከማሁ ግበሩ፤

እንዲህ አድርጉ፤

፳፩፡ ወይእዜኒ እምድኅረ ዝንቱ ሕይወት ይከውን ለእለ ይፈቅዱ ሠናየ ለፋርስ ወለእለ ኪያነ ይፈቅዱ ይዕልዉ ተዝካረ ሙስናሆሙ፤

አሁንም ይህ ሕይወት ከተደረገ በኋላ ለፋርስ ሰዎች በጎ ነገርን የሚወዱ እኛን ይወነጅሉ ዘንድ የሚወዱ ይጽሐፉ ያለበት ነው የጥፋታቸው መታሰቢያ የሚሆን ደብዳቤ ይጻፉ፤

፳፪፡ ወኵሉ ብሔር አው ሀገር ኵለሄ ዘኢገብረ፤

በከተማውም በገጠሩም ባራቱ ማዕዝን፤

ዘኢገብረ ከመዝ፤

እንዲህ ያላደረገ፤

በኵናት፤

በጦር፤

ወበእሳት፤

በእሳት፤

የሐልቅ በመዓት፤

በመዓተ እግዚአብሔር ይጠፋል፤

ወአኮ ለሰብእ ባሕቲቶሙ ዘይከውን ሙስና፤

ጥፋት የሚደረግ በሰዎች ብቻ አይደለም፤

አላ ለአራዊትኒ ወለአዕዋፍኒ ለዝሉፉ ይከውን፤

በአራዊትም በአዕዋፍም ፈጽሞ ይደረጋል እንጂ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፡ ወያርእይዋ ለይእቲ መጽሐፍ ገሐደ ይስፍሕዋ ወይርአይዋ፤

ይችን መጽሐፍ ባደባባይ ያሳ ይዋት፡ ሲያሳዩዋትም ዘርግ ተው ያሳዩዋት፡

ወይከውኑ ድልዋነ ኵሎሙ አይሁድ በይእቲ ዕለት ከመ ይትቀተሉ ፀሮሙ፤

ጠላታቸውን ያጠፉ ዘንድ አይሁድ ሁሉ በዚያች ቀን የተዘጋጁ ሆኑ፤

፳፬፡ ወወጽኡ እለ ይጼአኑ አፍራሲሆሙ እንዘ ይጔጕኡ ከመ ይግበሩ ትእዛዘ ንጉሥ፤

የንጉሡን ትእዛዝ ያደርጉ ዘንድ በፈረስ የተቀመጡ ሰዎች ፈጥነው ወጡ፡

ወተሠይመ ዝንቱ ትእዛዝ ውስተ ሱሳ ሀገር፤

ይህ ትእዛዝ ሱሳ በሚባል ሀገር ተደረገ፡

፳፭፡ ወወጽአ መርዶክዮስ እንዘ ልቡስ አልባሰ መንግሥት ዘበ አክሊለ ወርቅ፤

መርዶክዮስም ዝርግፍ ወርቅ አክሊለ ወርቅ ያለበት ልዩ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ ወጣ፡

ወጽንብል ሲራየ ሜላት፡

ሐር አጥላስ ሐር ጭንብል እንደ ኒሻን ያለ ነው፡

ወርእዩ እለ ውስተ ሀገረ ሱሳ ሀለዉ ወተፈሥሑ፤

ሱሳ በሚባል ሀገር ያሉ ሰዎች ይህን አይተው ደስ አላቸው፤

፳፮፡ ወለአይሁድሰ ኮነ ብርሃን ሎ[ሙ] ተፈሥሕት በበሀገሩ ወበበ ብሔሩ በነበ ተሠይመ ውእቱ ትእዛዝ፤

ለአይሁድ ግን ይህ ትእዛዝ በተደረገበት በከተማውም፤ በገጠሩም ተድላ ደስታ ሆነ፡

ውነበ ተረክበ ዝንቱ መጽሐፍ ዘፍሥሐ፤

ደስ የሚያሰኝ ይህ መጽሐፍ በተገኘበት ሁሉ ፍሥሐ ባለው ራፍቅ ይላል፡ ፍሥሐ ማለት ነው፡

ወጽጋበ ለአይሁድ፤

ለአይሁድ ጥጋብ የሚሆን፡

ወፍቅር ወሐሜት፤

ፍቅር ደስታ የሚሆን ይህ መጽሐፍ በተገኘበት ሁሉ እውቀት ተድላ ደስታ ይሆናል፡

፳፯፡ ወብዙኃን እለ አምኑ አሕዛብ ወእለ ተገዘሩ፤

አምነው የተገዘሩ አሕዛብ ብዙ ናቸው፡

ወተሐረሙ በእንተ ፍርሐቶሙ ለአይሁድ፤

አይሁድን ስለ ፈሩ ሥርዓት አደረጉ።



## ምዕራፍ ፲፩

፩፡ እስመ ዘ፲ቱ ወ፪ቱ አውራኅ አመ ፲ ወ ፫ ለወርኃ አዳር፤

ባሥራ ሁለተኛ ወር በመጋቢት፤ መጋቢት በባተ ባሥራ ሦስት ቀን፡

በጽሐ መጽሐፍ ዘጸሐፈ ንጉሥ፤

ባሥራ አራተኛ ይቱ ቀን ሊጠፉ፤ ባሥራ ሦስተኛ ይቱ ቀን ንጉሥ የጻፈው መጽሐፍ ደረሰ፡

፪፡ በይእቲ ዕለት ተሐጕሉ እለ ቆሙ ላዕለ አይሁድ፤

በዚች ቀን በአይሁድ ላይ በጠላትነት የተነሱ ሰዎች ጠፉ፡

ወአልቦ እንከ ዘቀተሎሙ ለአይሁድ፤

አይሁድን ግን ያጠፉቸው የለም፡

እስመ ይፈርህዎሙ፤

ይፈሯቸዋልና፡

፫፡ ወመላእክተ አሕዛብኒ፤

የአሕዛብ አለቆች፡

ወመገብትኒ፤

ሹማምንቱ፡

ወጸሐፍት፤

ጸሐፊዎች፡

ወአበይተ ንጉሥ፤

የንጉሥ መኳንንት፡

፬፡ ያከብርዎሙ ለአይሁድ በእንተ ፍርሀተ መርዶክዮስ ወይትሐዘቡ፤

መርዶክዮስን ስለተጠራጠሩ፤ ስለ ፈሩ አይሁድን እነዚህ ሁሉ ያከብሯቸዋል፡

እስመ መጽሐፈ ንጉሥ ተሠ ይመ በኵሉ መንግሥቱ፤

የንጉሥ ደብዳቤ በሚገዛው ሀገር ሁሉ ተገኝቷልና፡

፭፡ ወበሱሳ ሀገር ቀተሉ አይሁድ ፭ተ ፻ተ ወ፹፤

ሱሳ በሚባል ሀገርም አይሁድ አምስት መቶ ሰባ ሰው ገደሉ፡

፮፡ ኅራንሂ ወንጦን ወደላፎን ወፋስጋ ወፈርዶክታ ወቤርያ ወሰበርክ ወመርሶን ወአሮ ፎዮን ወኤርሴዎን ወዘበቴዮን ደቂቀ ሐማ ወልደ አምዶቱ ብግያዊ ፀላዒሆሙ ለአይሁድ፤

እኒህ አሥራ አንድ ናቸው፡ ላንዱ ሁለት ስም አለው፡ የአይሁድ ጠላታቸው የሚሆን የአምዶቱ ልጅ የሐማን ልጆች፡

ለአሠርቱሆሙ አኅዘዎሙ፤

አሥሩን ሁሉ ያዟቸው፤

ወበርበሩ በይእቲ ዕለት፤

በዚያች ቀን በዘበዙ፡

፯፡ ወዜነውዎ ለንጉሥ ኍልቈ ሰብእ ዘሞተ በሱሳ ሀገር፤

በሱሳ የሞተውን ሰው ቁጥር ለንጉሡ ነገሩት፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፡ ወይቤላ ንጉሥ ለአስቴር ቀተሉ አይሁድ በሱሳ ሀገር ፭ተ ፻ተ ወ፲ ዕደወ።

ንጉሥ አስቴርን አይሁድ በሱሳ አምስት መቶ ሰባ ሰው የገደሉ፡

፱፡ ወእፎ እንከ በአድያም፤

በዙሪያውም ምን ያህል ሰው የጠፉ ይሆን፡

ምንተ እንከ ታስተበቍዒ በቅድሜየ እግበር ለኪ።

አደርግልሽ ዘንድ በፊቴ እንግዲህ ምን ትለምኚለሽ፡

፲፫፡ ወትቤሎ አስቴር ለንጉሥ ሀቦሙ ለአይሁድ ከማሁ ከመ ይግበሩ ጌሠመ።

አስቴር ንጉሥን እንዲህ አለ ችው፡ ነገም እንደዚሁ ያደርጉ ዘንድ አይሁድን እዘዛቸው፡

ከመ ይስቅሉ አሠርቲሆሙ ደቂቀ ሐማ።

የሐማን ልጆች አሥሩን ሁሉ ይሰቅሏቸው ዘንድ፡

ወአዝዝ ከማሁ ይግበሩ።

እንዲህ ያደርጉ ዘንድ እዘዝ፡

፲፬፡ ወአዘዞሙ ለአይሁድ ለእለ ሀለዉ ውስተ ሀገር ይስቅሉ ሥጋሆሙ ለደቂቀ ሐማ።

በከተማ ያሉ አይሁድን የሐማን ልጆች ይሰቅሉ ዘንድ አዘዛ ቸው፡

፲፭፡ ወተጋብኡ አይሁድ ውስተ ሱሳ ሀገር አመ ፲ ወ፬ ለወርኀ አዳር እምሠርቅ።

መጋቢት በባተ በአሥራ አራተኛው ቀን አይሁድ በሱሳ ተሰበሰቡ ፡

ወቀተሉ ፫ተ ፻ተ ዕደወ።

ሦስት መቶ ሰዎችን ገደሉ፡

፲፮፡ ወእለ ተርፉ አይሁድ እለ ይትቀነዩ ለነገሥት።

ለነገሥት የሚገዙ በገጠር ያሉ አይሁድ፡

ተጋብኡ እሙንቱኒ በበይናቲሆሙ ወተራድኡ።

እነዚህም በየወገኖቻቸው ተሰብስበው ተረዳዱ፡

ወአልቦ ባሕቱ ዘበርበሩ።

ነገር ግን የበዘበዙት የለም፡

፲፯፡ ወአእረፉ እምቀትሎሙ።

ባሥራ አራተኛይቱ ቀን የገደሉት የለም፡

ወዘቀተሉሰ አመ፲ወ፫ ለሠርቀ አዳር ፲፻ወ፭፻።

መጋቢት በገባ ባሥራ ሦስት ቀን የገደሉት ግን እልፍ ከአምስት ሺህ ነው፡

ወአልቦ ዘበርበሩ እንከ አመ ፲ ወ፬ ለውእቱ ወርኅ።

መጋቢት በገባ ባሥራ አራት ቀን የበዘበዙት የለም፡



ወረሰይዋ ለይእቲ ዕለት በዓለ ከመ ባቲ ያዕርፉ ምስለ ትፍሥሕት ወጽጋብ፡

ከጥጋብ ከደስታ ጋራ ያርፉባት ዘንድ ይችን አሥራ አራተኛይቱን ቀን በዓል አደረጓት፡

፲፰፡ ወአይሁድ እለ ውስተ ሱሳ ሀገር ተጋብኡ አመ ፲ ወ፬።

በከተማው ያሉ አይሁድ ግን በዚች ባሥራ አራተኛይቱ ቀን ተሰበሰቡ፡

ወኢያዕረፉ ይእተ አሚረ።

ያን ጊዜ ከመግደል አላረፉም፡

ወአመ ፲ ወ፭ ገብሩ በዓለ ወትፍሥሕተ።

ባሥራ አምስተኛይቱ ቀን በዓል ተድላ ደስታ አደረጉ፡

፲፱፡ ወበበይነ ዝንቱ ነገር አይሁድ እለ ተዘርዉ ውስተ ኵሉ በሐውርት ቅሥፊ ሠናየ ገብርዋ ለይእቲ ዕለት።

ዕረፍተ ሠናየሲል ነው። አንድም ቅሥፊ በአፍዓ ያሉት በአሥራ አራተኛው ቀን በዓል አደረ ጓት፡

አመ ፲ ወ፬።

ስለዚህ ነገር በየሀገሩ ተበትነው በአፍአ ያሉ አይሁድ አሥራ አራተኛይቱን ቀን በዓል አደረ ጓት፡

ወጽጋበ እንዘ ይፌንዉ ለቢጾሙ ወለጉሮሙ ወለእለ ይነብሩ ውስተ ደብረ አህጉሪሆሙ።

ለባልንጀሮቻቸው፣ ለጎረቤቶ ቻቸው በሀገራቸው ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ገንዘባቸውን እየሰ ደዱ ተድላ ደስታ አደረጉ፡

ወአመ ፲ወ፭ ገብሩ ትፍሥሕተ ሠናየ እንዘ ይፌንዉ ክፍለ ለቢጾሙ ወለጉሮሙ፡

ለጎረቤቶቻቸው፣ ለባልንጀሮ ቻቸው ፈንታቸውን እየላኩ ባሥራ አምሥተኛይቱ ቀን ተድላ ደስታ አደረጉ፡

፳፡ ወጸሐፎ መርዶክዮስ ለዝንቱ ነገር ውስተ መጽሐፍ።

መርዶክዮስ ይህን ነገር በመጽሐፍ ጽፎ፤

ወፈነዎ ለአይሁድ እለ ሀለዉ ውስተ መንግሥተ አርጤክስስ ለቅሩባን ወለርኁቃን፡

አርጤክስስ በሚገዛው ሀገር ላሉ በሩቅም በቅርብም ለሚኖሩ ለአይሁድ ሰደደላቸው፡

ከመ ይግበርዎሙ ለእሉንቱ።

መዋዕል በአለ፡

አመ፲ቱ ወ፬ቱ ወአመ ፲ወ፭ቱ ለወርኀ አዳር።

እነዚህን በዓላት በመጋቢት ባስራ አራተኛይቱና ባስራ አምስተኛይቱ ቀን በዓል ያደርጉ ዘንድ፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፡ እስመ በእማንቱ መዋዕል አዕረፉ አይሁድ እምነ ፀሮሙ ወጸላዒሆሙ።

ባሥራ አራተኛውና ባሥራ አምስተኛው ቀን አይሁድ ከጠላቶቻቸው አርፍዋልና ፡

በወርኀ ዘቦቱ ገብኡ እምነ ላህ ውስተ ትፍሥሕት።

ከሀዘን ወደ ደስታ በተመለሰበት ወራት ፡

ወእምነ ሕማም ውስተ ትፍሥሕት።

ከመከራ ወደ ደስታ በተመለሰበት ወር፤

ዘውእቱ አዳር።

ይኸውም ወር መጋቢት ነው፤

ወገብርዎ በኵሉ መዋዕሊሆሙ ከብካበ ወጽጋበ።

ባለ በዘመናቸው ሁሉ ሠርግ ጥጋብ አደረጉት፤

ወይጼግዉ ለምስኪናን ወለዘተ አኀዊሆሙ።

ለድሆች ለወንድሞቻቸው ገንዘብ እየሰጡ፤

፳፫፡ ወተወክፉ አይሁድ በከመ ጸሐፈ ሎሙ መርዶክዮስ።

አይሁድ መርዶክዮስ እንደጻፈ ላቸው ተቀበሉ፤

፳፬፡ ዘከመ ቀተሎሙ ሐማ ወልደ አምዳቱ መቄዶንያዊ።

ከጠንቋዮች ወገን የሚሆን የአምዳቱ ልጅ ሐማ እንደ ገደላቸው፤

በከመ ሐሰበ ወአስተቃሰመ ለአማስኖቶሙ።

እነዚያን ለማጥፋት እንዳሰበ እንዳሟረተ፤

፳፭፡ ወዘከመ ቦአ ኀበ ንጉሥ።

ከንጉሥ እንደገባ፤

ወሰአሎ ከመ ይስቅሎ ለመርዶክዮስ።

መርዶክዮስን ይሰቅሉት ዘንድ እንደለመነው ጻፈላቸው ፡

ወኵሉ ዘሐለየ ከመ ይግበር እኩየ ላዕለ አይሁድ ገብአ ላዕለ ርእሱ።

በአይሁድ ላይ ያደርገው ዘንድ ያሰበው ክፉ ነገር ወደ ራሱ ተመለሰ፤

ወተሰቅለ ውእቱ ወደቂቁ።

እሱም ልጆቹም ተሰቀሉ፤

፳፮፡ ወበበይነ ዝንቱ ተሰምየ እማንቱ መዋዕለ ድኅነት።

ስለዚህ ነገር እነዚህ ዕለታት ድኅነት የተደረገባቸው ቀኖች ተባሉ፤

በእንተ ዘተአዕዋ፤

እፃቸው ዕፃ ሞት ዕፃ ሕይወት ስለ ተደረገላቸው፤

እስመ በነገሮሙ ይሰምይዎን ድኅነ።

በቋንቋቸው ድኅነት የተደረ ገባቸው ዕለታት ይሏቸዋልና ፡

በእንተ ቃለ መጽሐፍ።

ይህች መጽሐፍ ስለ ተናገረች፤



ወበእንተ ኵሉ ዘረከቡ ውስቴታ።

በሷ ውስጥ ስላገኙት ሁሉ፤

ወኵሉ ዘኮነ ላዕሌሆሙ፤

በሳቸው ላይ የተደረገውን፤

፳፯፡ ወበዘጸሐፉ ወአውከፉ አይሁድ።

የተጻፈውን አይሁድ የተቀበሉትን፤

ሎሙ ወለዘርዖሙ።

ለራሳቸውም ለልጆቻቸውም ፡

ወለዘይደመር ምስሌሆሙ።

ከርሳቸውም ጋራ በሃይማኖት አንድ ለሚሆኑ፤

ከመ ኢይፍልሱ እምዝንቱ።

ከዚህ ሥርዓት እንዳይወጡ፤

ወእላንቱ መዋዕል ተዝካረ ይትገበሩ ለዓለመ ዓለም፤

እኒህ ቀኖች ለዘለዓለም መታሰቢያ ይሁኑ፤

በበአህጉር ወበበሐውርት ወነገድ፤

ቤት ሠርተው በሚኖሩ በየሀገሩ በነገደ ሴም በነገደ ካም በነገደ ያፌት መታሰቢያ ይሁኑ፤

፳፰፡ ወእማንቱ መዋዕል ይትገበሩ ተዝካረ ለዝሉፉ።

እኒኽም ዕለታት ሁልጊዜ መታሰቢያ ይሁኑ፤

እስመ ቦቱ ድኅኑ እስራኤል።

እስራኤል ከሞት ድነውባቸዋልና፤

ከመ ኢይደምስስ ተዝካሮሙ ለዓለም።

ለዘለዓለሙ መታሰቢያቸው እንዳይጠፋ፤

፳፱፡ ወጸሐፈት አስቴር ወለተ አሚናዳብ።

የአሚናዳብ ልጅ አስቴር ጻፈች፤

ወመርዶክዮስ አይሁዳዊ ኵሎ ዘገብረ፤

አይሁዳዊ መርዶክዮስ ያደረገ ውንም ጻፈች ፡

ወአጽንኡ መጽሐፈ ዘመድኀኒት።

ድኅነት የተደረገበትን መጽሐፍ ጸኑ፤

፴፩፡ ወመርዶክዮስሰ ወአስቴር ንግሥት አሕረምዋ ሎሙ አሚሁ።

መርዶክዮስና አስቴር ግን ያን ጊዜ ሥርዓት አደረጓቸው፤

ወመሐሉ በሕይወቶሙ ወምክሮሙ፤

ሕይወት ይንሳን ምክር ይንሳን ብለው ማሉ፤

፴፪፡ ወአስቴርኒ በቃላ ለዓለም ወተ ጽሕፈ ለተዝካር።

አስቴርም ለዘለዓለም መታሰ ቢያ ሊሆን ቃሏን ይዝጋው ብላ ማለች፤ አንድም ቃሏን አስምታ ተናገረች።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲፪

፩፡ ወጸሐፈ ንጉሥ ውስተ መንግሥቱ ዘበምድር ወዘባሕር፡

ንጉሥ በሚገዛው ሀገር ለከተማ ውም ለገጠሩም ጻፈ፡

፪፡ ወላዕለ ጽንዑ፣

ለጽኑአኒሁ ሲል ነው፣ ለጽኑ አን ጻፈ፡

ወቀትሎሙ፣

ወመስተቃትላኒሁ ሲል ነው፣ ለአርበኞች፡

ወላዕለ ክብሮሙ ወብዕሎሙ ለብዑላኒሁ፣

ወለክቡራኒሁ ሲል ነው፤ ለባለጸጎች ለከበሩት፡

ወመንግሥቱ፣

ወለነገሥት ዘታሕቴሁ ሲል ነው፣ ከበታቹ ላሉ ነገሥታት፡

ናሁ ልኩዕ ውስተ መጽሐፈ ፋርስ ወሜዶን ለተዝካር፣

ለነዚህ ሁሉ መታሰቢያ ሊሆን በፋርስና በሜዶን መጽሐፍ እነሆ ተጽፏል፤

፫፡ ወመርዶክዮስ ባሕቲቱ የአቅብ መንግሥተ ንጉሥ አርጤክስስ ዓቢይ ውእቱ፣

መርዶክዮስ ግን ገናና የሚሆን የአርጤክስስን መንግሥት ይጠብቅ ነበረ፡

ወመንግሥቱኒ ክቡር ውእቱ በኀበ አይሁድ ወይትፈቀድ፣

መንግሥቱም በአይሁድ ዘንድ የሚከብር የሚወደድ ነው፤

ወይነግር ንብረታ መርዶክዮስ ለኵሉ ሕዝብ በትውልዶሙ፣

መርዶክዮስ የዚችን መንግሥት ታሪኳን በዚህ ጊዜ እንዲህ ተደረገ እያለ ለሕዝቡ ሁሉ በየትውልዳቸው ይነግራል፤ በትውልዶሙ ባለው በበድሮሙ ይላል አብነት፡

፬፡ ወይቤ መርዶክዮስ እምነ እግዚአብሔር ኮነ ዝንቱ ነገር፣

መርዶክዮስ ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዞ ሆነ አለ፤

፭፡ ተዘከርኩ በእንተ ሕልም ዘርኢኩ በበይነ ዝንቱ፣

ስለዚህ ነገር ያየሁት የህልሙን ነገር አሰብኩ፤

እስመ ኢሐለፈ ዕድሜሁ ለውእቱ ሕልም፣

ከሕልሙ አንድ ነገር አልቀረምና፤ አንድም እምዕድሜሁ ይላል በጊዜው ጊዜ ተደርጓልና፤

፮፡ እንታክቲ ንስቲት፣

ነቅዓ ማይ ያላት አስቴር ናት፡

እንተ ኮነት ፈለገ፣

ንጉሥ አገባት፡



ወኮነ ብርሃነ ፀሐይ፣

እቴጌነት አደረሰላት፡ ማይ ብዙኅ ያለውን አስቴር ናት ብሎ ተረጉመው፡

ወፈለግ እንተ አውሰባ ንጉሥ፣

ፈለግ ያለውን ያገባት አርጤክስስ ነው ብሎ ተረጉመው፤

ወረሰዮ ንግሥተ፣

ብርሃነ ፀሐይ ያለውን ረሰዮ ንግሥተ ብሎ ተረጉመው እቴጌነት አደረሰላት፤ ደግ መጽሐፍ ከሆነ በ፫መረበት ይጨርሳልና፤

፯፡ እልክቱሰ ክልኤቱ አክይስት አነ ወሐማ ንሕነ፣

ሁለት ዘንዶዎች የተባልን እኔና ሐማ ነን ይላል መርዶክዮስ፤

፰፡ ወአሕዛብኒ እለ ተጋብኡ ከመ ያማስኑ ስሞሙ ለአይሁድ፣

የአይሁድን ስማቸውን ያጠፉ ዘንድ የተሰበሰቡ አሕዛብ የተባሉም፡

፱፡ ወሕዝበ ዚአየ ፳ኤል፣

የኔ ወገኖች የሚሆኑ እስራኤል ናቸው፤

እለ ያአወይዉ ኀበ እግዚአብሔር ወድኅኑ፣

ከእግዚአብሔር ዘንድ ለምነው የዳኑ ናቸው፡

ወአድኀኖሙ እግዚአብሔር ለሕዝቡ፡

ወገኖቹን እግዚአብሔር አዳና ቸው፡

ወአድኀነነ እግዚአብሔር እምነ ዝንቱ ኵሉ እኩይ፤

እግዚአብሔር ከዚህ ከክፉ መከራ ሁሉ አዳነን፤

፲፡ ወገብረ እግዚአብሔር ዓቢየ መድምመ ወተአምረ ዘኢኮነ ከማሁ በውስተ አሕዛብ፡

እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ተደርጎ የማይታወቅ ድንቅ ገናና የሚሆን ተአምራት አደረገ፤

፲፩፡ ወበበይነ ዝንቱ ገብረ ፪ኤተ ክፍለ፣

ስለዚህ ነገር ሁለት ክፍል አደረገው፤

ዕፃ ሞት ዕፃ ሕይወት፣

ክልኤተ ክፍለ ባለው አሐደ ክፍለ ይላል፤

አሐዱ ለሕዝበ እግዚአብሔር፡

ዕፃ ሕይወት፤ ለእግዚአብሔር ወገኖች ለእስራ ኤል ነው፡

ወአሐዱ ለካልዕ ሕዝብ፡

አንዱም ዕፃ ሞት ለሁለተኛው ወገን ነው፡

፲፪፡ ወበጽሐ እልክቱ ክልኤቱ ክፍል በሰዓት ወበጊዜ፤

በሰዓት በጊዜው ጊዜ እኒህ ሁለቱ ክፍል ደረሱ፡

በዕለተ ደይን ቅድመ እግዚአብሔር፡

በቁርጥ ፍርድ ቀን በእግዚአ ብሔር ፊት ተደረገ፤

ወላዕለ ኵሉ አሕዛብ፣

ዕፃ ሞት፣ በአሕዛብ ላይ ተደረገ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፡ ወተዘከሮሙ እግዚአብሔር ለሕዝቡ፤

እግዚአብሔር ወገኖቹን በረድኤት አሰባቸው፡ ዕፃ ሕይወት ወጣላቸው፡

ወአንጽሐ ርስቶ፤

ማደሪያው እስራኤልን ከኃጢአት አነጻው፡

፲፬፡ ወከና እማንቱ መዋዕል በወርኀ አዳር አመ ፲ወ፬አመ ፲ወ፭ ለውርቀ ውእቱ ወርኅ፤

ዕፃ ሞት፤ ዕፃ ሕይወት የተደረገባቸው እነዚህም ቀኖች መጋቢት በባተ ባሥራ አራተኛ ባሥራ አምስት ቀን ሆኑ፡

እንዘ ይትጋብኡ በትፍሥሕት ቅድመ እግዚአብሔር በትውልደሙ ለዓለም ውስተ እስራኤል፤

ሕዝቡ ደስ ብሏቸው በወገኖቹ በእስራኤል ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ተሰብስበው በዘመናቸው በዓል አደረጉ።

## ምዕራፍ ፲፫

፩፡ ወአመ ራብዕት አመተ መንግሥቱ ለጰጠሎሜዎስ፤

ጰጠሎሜዎስ በነገሠ ባራተኛ ዘመን፡

ወቀለዮጰጥራ አብዶስ እግዚአብሔር፤

ካህነ እግዚአብሔር ሲል ነው፡ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ቀለዮጰጥራ በተሾመ ባራተኛው ዘመን፡

ይቤ ርእኩ ካህነ ዓቢየ እንዘ ይጽሕፍ፤

ደጉን ካህን ሲጽፍ አየሁት አለ፡ እሱ ራሱን አርቆ ይናገራል፡

፪፡ ወሌዋዊ ጰጠሎማዊ ይትወፌይ መጽሐፈ እንተ ባቲ ድኅኒን እንተ ይቤሎ ሀለወት ሌዋዊ ጰጠሎማዊ፤

ድኅነት ያለባት ከኔ ዘንድ አለች ያለውን የአስቴርን መጽሐፍ ተቀብሎ፡

፫፡ ወተርጒማ ለሲማኮስ ጰጠሎማዊ ዘእምነ ኢየሩሳሌም፤

ከኢየሩሳሌም ወገን ለሚሆን ለሲማኮስ ጰጠሎማዊ፡ መለሰላት አስቴር በፋርስ ቋንቋ ተጽፋ ትኖር ነበር፡ ኋላ በእብራይስጥ ቋንቋ መልሶ ለዕቃቤቱ ለሲማኮስ እናቲቱንም ልጅቱንም ሰጠው፡ አንድም ወአመ ራብዕት ብለህ መልስ፡ የቀረው አይለ ወጥም፡ ሌዋዊ ጰጠሎማዊ ድኅነት የሚገኝባት ከኔ ዘንድ አለች ያለውን አሳልፎ ቀዳት እናቲቱን ለዕቃቤቱ ለሲማኮስ ሰጠው፡ ልጅቱንም ለጰጠሎማዊ ልጅ ሰጠው።

ተፈጸመ መጽሐፈ አስቴር በሰላመ እግዚአብሔር በረከተ ጸሎታ የሃሉ ምስሌነ፤

ወስብሐት ለ እ ግ ዚ አ ብ ሐ ር ለዓለመ ዓለም አሜን።



# የአስቴር ገባዔ ፳ ነው

## የመጽሐፈ ሰሎሞን ገባዔ


፩ኛ ገባዔ ታሪክ፡

፪ኛ ገባዔ ምሳሌያተ ሰሎሞን፡

፫ኛ ገባዔ ምሳሌያተ ጥበብ በፍናው ትትፌሣሕ፡

፬ኛ ገባዔ ምሳሌያተ እግዚአብሔር በጥበብ ሣረረ፡

፭ኛ ገባዔ ምሳሌያተ ማዕከለ ማኅበር ወሰንግሊጋ ስተይ ማየ እምቀሱትከ፡

፮ኛ ገባዔ ምሳሌያተ በላ ለጥበብ እኅተ ዚአየ፡

፯ኛ ገባዔ ምሳሌያተ እግዚአብሔር ፈጠረኒ ቀዳሜ ኵሉ ተግባሩ፡

፰ኛ ገባዔ ምሳሌያተ ብእሲት ኄርት ታኀሥእ ለምታ ግብረ፡

፱ኛ ገባዔ ምሳሌያተ ዐ እለ ያሌዕሉ ርእሶሙ፡

፲ኛ ገባዔ ምሳሌያተ ጠባባት አንስት፡

፲፩ ገባዔ ምሳሌያተ ትምህርተ የዋሃን ይትዐወቅ፡

፲፪ ገባዔ ምሳሌያተ ሰገል ውስተ አፈ ንጉሥ፡

፲፫ ገባዔ ምሳሌያተ ዐቢወ ማይ ቀዳሚ ጽልዕ፡

፲፬ ገባዔ ምሳሌያተ ዘረከበ ብእሲተ ኄርተ፡

፲፭ ገባዔ ምሳሌያተ ለሀገር ጽንዕት ቦአ ጠቢብ፡

፲፮ ገባዔ ምሳሌያተ አውጽእ ቀታሌ ነፍስ፡

፲፯ ገባዔ ምሳሌያተ ዕዕድ ስቆርት፡

፲፰ ገባዔ ምሳሌያተ ለአለቅት ሠላስ አዋልድ፡

፲፱ ገባዔ ምሳሌያተ ተግማዐ ሰሎሞን፡

፳ ገባዔ ምሳሌያተ ከመ ከልብ ዘይገብዕ ዲበ ቂያዑ፡

፳፩ ገባዔ ምሳሌያተ አእምሮ አእምር፡

፳፪ ገባዔ ምሳሌያተ ጥበበ ሰሎሞን፡

፳፫ ገባዔ ምሳሌያተ ንቅትሎ ለጻድቅ፡

፳፬ ገባዔ ምሳሌያተ አሚሃ ይቀውም ጻድቅ፡

፳፭ ገባዔ ምሳሌያተ ምንት ይእቲ ጥበብ፡

፳፮ ገባዔ ምሳሌያተ በማኅበር አስተርአየ ኄረ፡

፳፯ ገባዔ ምሳሌያተ ዛቲ ዐቀበት አበ ዓለም፡


www.ethiopianorthodox.org

፳፰ ጉባዔ ምሳሌያተ ወገዐረ ተዝካር፡

፳፱ ጉባዔ ምሳሌያተ እስመ ለቀደምት፤

፴ ጉባዔ ምሳሌያተ ወእመቦ ዐራቢ ዕፀ ዘያስተርኢ፡

፴፩ ጉባዔ ምሳሌያተ ወአንተሰ አምላክነ ኄር፤

፴፪ ጉባዔ ምሳሌያተ በረድኒ ወአስሐትያ ቆሙ ወጸንዑ፡

፴፫ ጉባዔ ምሳሌያተ ለእንታክቲ ሌሊት አእመ ርዋ አበዊነ፡

፴፬ ጉባዔ ምሳሌያተ ቃለ መክብብ፡

፴፭ ጉባዔ ምሳሌያተ ቦ ለኵሉ ዘመን፡

፴፮ ጉባዔ ምሳሌያተ ዕቀብ እገሪከ፡

፴፯ ጉባዔ ምሳሌያተ ይኄይስ ስም ሠናይ እምቅብዕ መዓዛ፤

፴፰ ጉባዔ ምሳሌያተ ነዓ ብላእ ኅብስተከ፡

፴፱ ጉባዔ ምሳሌያተ አሌ ለኪ ሀገር እንተ ንጉሥኪ ወሬዛ፤

## የመጽሐፈ ዳንኤል ጉባዔ

፩ ጉባዔ ታሪክ፡

፪ ጉባዔ ወሀሎ አሐዱ፡

፫ ጉባዔ አመ ሠላሳ ዓመተ መንግሥት፤

፬ ጉባዔ በካልዕ ዓመተ ዓመት መንግሥት፤

፭ ጉባዔ አመ አሠርቱ ወሰመንቱ፤

፮ ጉባዔ መቆመ አዛርያ፤

፯ ጉባዔ ወኢሕደጉ ወዓልት፡

፰ ጉባዔ ይቤ ናቡከደነፆር፡

፱ ጉባዔ ብልጣሶር ገብረ ለመገብቱ፤

፲ ጉባዔ ወዳርዮስ ሜዶናዊ ነግሠ፤

፲፩ ጉባዔ በቀዳሚ ዓመተ መንግሥቱ ለብልጣሶር፡

፲፪ ጉባዔ ወአመ አሠርቱ ወሠለስቱ ዓመተ መንግሥቱ ለብልጣሶር፡

፲፫ ጉባዔ በቀዳሚ ዓመተ መንግሥቱ ለዳርዮስ፡

፲፬ ጉባዔ በሠላስ ዓመተ መንግሥቱ ለቂሮስ፡

፲፭ ጉባዔ ታሪክ ወአነ በዓመት ቀዳሚ ዘዳርዮስ፡

፲፮ ጉባዔ ወወለተ አንስትያ ትትወነብ፡

፲፯ ጉባዔ ወውእተ አሚረ ይትነሣእ ሚካኤል መልአክ፡

፲፰ ጉባዔ እምድኅረ ሞተ እስጥያኪስ፡

# መጽሐፈ ኢዮብ

## መቅድም ፤

ኢዮብ ማለት አበባ ፣ ጨረቃ ማለት ነው፡ አሕዛብ ለልጆቻቸው ስም ሲያወጡ በአማረ በአማረ ነገር ነውና፣ ይህም ኢዮብ አብርሃምን የሚመስልበት፣ ከአብርሃም የሚበልጥበት ግብር አለው፡ አብርሃምን የሚመስልበት አብርሃም እንግዳ ይቀበል ነበር፤ ኢዮብም እንግዳ ይቀበል ነበር ፤

ወለኵሉ ዘመጽአ ርኅው አንቀጸ ቤትየ ፣

ዋኅተ ቤትየም ይላል፤ ወበአፍአ ኢኀደረ ነግድ ብሎ እንዲያ መጣው ከአብርሃም የሚበልጥበት ግብር አብርሃም ሚስቱ ማራ ሳለች ከአጋር እስማኤልን ወልዷል፤ ሚስቱ ከሞተች በኋላም ከኬጡራ ፯ ልጆች ወልዷል፤ ኢዮብ ግን ሚስቱ፣ ባርከ ለእግዚአብሔር ወሙት፣ ብላ በዚህ ምክንያት ብትቀሠፍበት እንደ ዘመነ ሐዲስ በአንዲት ፀንቶ የሚኖር ሁኗል ፣ ይህም ኢዮብ ጥመት የሌለበት ቅን፣ ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ፣ ሐሰት የሌለበት እውነተኛ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ፤ የሚያመልክ በፍጹም ልቡናው ከክፉ ሥራ ሁሉ የሚርቅ ደግ ሰው ነበር ፯ ወንዶች ልጆች ፫ ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ አሁን ግምብ ተንዶ አጠፋቸው የሚል ነውና እንደ አርእስት ተናግሮታል፤ ፯ ሺህ የከብት መንጋ ነበረው ፤ አንድ ሁለት ብሎ ቆጥሮ፤ አንድም በረቱን ቆጥሮ ፫ ሺህ የበግ መንጋ ነበረው ፤ አንድ ሁለት ብሎ ቆጥሮ፤ አንድም በረቱን ቆጥሮ ፭፻ ግመል፣ ፭፻ ጥማድ በሬ፣ ፭፻ ባዝራ ወደልጋዝም ይሉታል ፤ ይህን ያህል ገንዘብ ነበረው፤ ባሮቹም እጅግ ብዙ ነበሩ፤ አሳርሶ አስነግዶ የሚያገኘው እጅግ ብዙ ነበር ፤ አንድም ኅታው ፣ ኅተራው፣ እረኞቹ ብዙ ነበር፤

ወውእቱሰ ብእሲ ኄር በብሔረ ጽባሕ በምሥራቀ ፀሐይ ፣

ኢዮብ ግን በፀሐይ መውጫ በምሥራቅ የሚኖር ደግ ሰው ነበር፤ አንድም እምሥራቀ ፀሐይ ይላል፤ በፀሐይ መውጫ ከነበሩ ሰዎች ይልቅ በብሔረ ጽባሕ የሚኖር ደግ ሰው ነበር ፤

ወየሐውሩ ደቂቁ ወይትጋበኡ ኅቡረ፣

ልጆቹ ሒደው በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር፣ ከባለጌ ልጅ ሲለይ ነው፤ የባለጌ ልጅ የሆነ እንደሆነ አንዱ ሲወጣ አንዱ ሲገባ ነው፡ እሱ ግን ሠርቶ፣ ቀጥቶ አሳድጓቸዋልና በአንድነት ይወጡ ይገቡ ነበር ፤

www.ethiopianorthodox.org